የአምላክ አዳኝ/መድኃኒት ማለት ነው /ማቴ. 1:21፣ የሐዋ. 2:34-36፣ ኤፌ. 1:20-21፣ ሉቃ. 2:11፣26፣27/::

የእግዚአብሔርን የማዳን ስሞች ሁሉ ያካተተ ስለሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ታላቅ የሆነ አዳኝ ስም ነው:: ዛሬ እግዚአብሔር በማዳን ኃይሉ ተገልጦ እስራኤላዊ የሆነውን የሰውን ፍላጎት የሚያሟላው ታላቅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው:: ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ማዳኑን ሊገልጥበት የመረጠው አዳኝ ነው:: /ኢሳ. 42:1-7/ ከዚህ የተነሣም በብሉይ ኪዳን የተዘገቡ የእግዚአብሔር የማዳን ስሞች ሁሉ ወደ እርሱ የሚያመለክቱ ናቸው:: በመጨረሻም አዳኝ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውስጥ ተጠቃለዋል:: አንዲህ ተብሎ ተጽፎአል:-

> *እግዚአብሔርም ሙላቱ ሁሉ በእርሱ ይሆን ዘንድ ወዶአልና... (ቆላ. 1:19)*
>
> *የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ ይኖራልና... (ቆላ. 2:9)*

ምዕራፍ አምስት

አስተምህሮተ ሥላሴ /Doctrine of Trinity/

መግቢያ

አስተምህሮተ ሥላሴ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪና ወሰን የለሽ አምላክ ራሱን የገለጠበት ትምህርት ነው:: ይህ አስተምህሮ ጠሊቅና ከባድ ነው:: ገደብ የሌለው አምላክ የተገለጠበት ስለሆነ ከተገደበው የሰው አእምሮ በላይ የሳቀ ነው:: ስለዚህ ውስን የሆነው የሰው እውቀት ሊደርስበትና ሊገመግመው የማይቻለው ነው:: በምድራዊ ቋንቋም መንፈሳዊ ይዘቱን እንደልብ ተንትኖና ገላልጦ ለማሳየት አይቻልም::

ከቀደሙት አባቶች መካከል አንዳንዶቹ የሥላሴን ጉዳይ ጠልቆ ሰማወቅ መሞከር ውቅያኖስን ቀድቶ ለመጨረስ እየጨለፉም ለመጨለጥ እንደ ማለብ ነው ብለዋል:: ይህ ትክክለኛ የሆነ አባባል ነው:: ምክንያቱም ሰዎች ከሚሠሯቸው ሥራዎች ሁሉ የሥላሴን ጉዳይ ከመመርመር የሰፋና የከበደ የለምና ነው:: ምሥጢረ ሥላሴ የሚለው ስያሜም ይህን ክብደት ተክትሎ የመጣ መሆኑን ልንገነዘብ እንችላለን:: ምሥጢሩም የሥላሴን ምንነት በጥልቀት ለማወቅ የሚቻል አለመሆኑ ነው::

ከላይ እንደተገለጸው፣ አስተምህሮተ ሥላሴ ከባድ ቢሆንም፣ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ትክክለኛ አቅጣጫን ተከትሎ ማጥናት ይቻላል:: ይህን ማድረጋችን ከሥላሴ አካላት ጋር ያለንን መንፈሳዊ ሕብረት እንድንረዳው ያስችለናል:: መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የመጨረሻው መገለጥ ነው:: ስለሆነም የሥላሴን አካላት፣ አንድነትና ሦስትነትን በተመለከተ በቂ መረጃዎችን ይዟል:: ከዚህ አኳያ የእኛ ድርሻ የሚሆነው እነዚህን መረጃዎች መሉ በሙሉ በጥንቃቄ ማየቱ ነው:: ሁልጊዜም ቢሆን ስለ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ጎብረት ስናጠና ይህን አካሄድ ማረጋገጥ ይኖርብናል::

ጥናታችን የሚያተኩርበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ግማሹን ብቻ አይተን ሌላውን ወደ ጎን መተው ወደ ስሕተት ሊመራን ይችላል:: የስሕተት

ትምህርቶችንም ብንመለከት የያዙት ሐሰት ብቻ ሳይሆን አውነትንም ጭምር ነው። አደገኝነታቸውም ሙሉ በሙሉ ስሕተት መሆናቸው ሳይሆን ይህን የመሰለ የአውነትና የስህተት ትምህርቶችን አጣምረው መያዛቸው ነው። አውነት በሆነው በኩል ለዎችን የመሳብ ሥራ ሲሠሩ ሐሰት በሆነው በኩል ደግሞ ከአውነት እንዲንሸራተቱ ያደርጋሉ።

የተጠቀሰውን አደጋ ሰመከላከል የሚቻሰው ስለ ሥላሴ የሚጠቅሷቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሙሉ በጥልቀት በመፈተሽ ነው። በዚህን ጊዜ ብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ያገኘበትንና መለኮታዊ አካላትን በጉልህ ያስተዋወቀውን አዲስ ኪዳንን መሠረት ማድረጉ አስፈላጊ ነው። በዚህ መሠረት ሳይ በመሆን ብሉይ ኪዳን ስለ ሥላሴ የሚሰውን አሳብ መመልከት ደግሞ ሌላው አስፈላጊ ነጥብ ነው። ይህን ስናደርግ አግዚአብሔር በመለኮት አካላት /አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ/ መካከል ያሰውን የሕብረት ምስጢር በመንፈሱ ብርሃን አንዲያሳየን መጻሰይ ይኖርብናል።

1. የአሐዱ ሥሉስነት ትርጉም

አግዚአብሔር አንድ ነው። አንዱ አግዚአብሔር ሦስት አካላት አሉት። አነርሱም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። አነዚህ ሦስቱ አካላት አንዱ የመለኮት ባሕርይ የሚገለጥባቸው ስለሆነ፣ አንደ ሦስት ስዎች የተነጣጠለ ሦስትነት የላቸውም። አያንዳንዱ አካልም የመለኮት ሙላት ያለውና ሙሉ አግዚአብሔር ነው /አግዚአብሔር አብ፣ አግዚአብሔር ወልድ፣ አግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ/።

ግንኙነታቸውን ተከትሎ መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ አብ /አባት/፣ ወልድ /ልጅ/፣ መንፈስ /መንፈስ ቅዱስ/ በማለት ይለይማል። በሦስቱም መካከል «እኔ»፣ «አንተ» እና «አርሱ» መባባል አስ። ሦስቱም ከዘለዓለም ናቸው። ሦስቱም ደግሞ በመለኮት፣ በክብር፣ በባሕርይ መገለጫዎች አንድ ስለሆኑ በህልውናቸው /በመኖራቸው፣ በመሆናቸው/ አይበላለጡም። መብለጥ ወይንም ማነስ በመካከላቸው

የለም። እግዚአብሔር አይከፋፈልምና አነርሱ የአርሱ ሦስት ክፍሎች አይደሉም።

2. «ሥላሴ» የሚለው ቃል ታሪካዊ አመጣጡና ጠቀሜታው

ሥላሴ የሚለው ቃል የግአዝ ቃል ነው። ትርጉሙም ሦስትነት ማለት ነው። ይህንንም ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ አናገኘውም። ይሁን አንጂ በትምህርተ መለኮት ግልጋሎት ሳይ በመዋል ረገድ ረጅም ጊዜን አሳልፏል። ይኼውም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን የአግዚአብሔርን መለኮታዊ አንድነትና ሦስትነት ይገልጻል ተብሎ በመታመኑ ምክንያት ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይህ ቃል በአንዱ አግዚአብሔር ሦስት አካላት አንዳሉ ያመለክታል የሚለው አስተሳሰብ በአጅጉ ተቀባይነት አንዳገኘ ከታሪካዊ ጠቀሜታው አንጻር መረዳት ይቻላል። ሥላሴ የሚለው ቃልም መጽሐፍ ቅዱስ የዘገበውን ይህን የአውነት ቃል አጎላው አንጂ አንግዳ የሆነ ትምህርትን አሳስከተለም።

አስተምህሮተ ሥላሴን ግልጽ ለማድረግ ቃሉን በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጥቅም ላይ ያዋለው የስነ መለኮት ምሁር የነበረው ለሜን አፍሪካዊው ተርቱሊያን ነበር። ከርሱም በመቀጠል የአንጾኪያ ጳጳስ የነበረው ቴምፍሎስ ይህን አስተምህሮ በማካሄድ ቀጣይነት አንዲኖረው አንዳደረገ ይታመናል። በዚሁ መሠረት ሁሰቱ አባቶች የመጀመሪያዎቹ በመሆን ተርቱሊያን በሳቲን ቋንቋ «ትርንታስ» /በአንግሊዝኛ /Trinity/ እና ቴምፍሎስ ደግሞ በግሪክ ቋንቋ «ትሪአስ» በማለት ስለ አግዚአብሔር አያስተማሩ የአካሳትን ሦስትነት ለመግለጽ ተጠቀሙበት።

ከሳይ ከተጠቀሱት አባቶች ዘመን ጀምሮ ቀጣዮቹ የቤተክርስቲያን አባቶች የላቲኑንና የግሪኩን ቃላት በመጠቀም የአግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚያመሰክተውን ትምህርት የበለጠ አሰፋፍተውት ነበር። አንደ ግሪኩና ላቲኑ ቃላት ሁሉ ሥላሴ የሚለውም የግአዙ ቃል ስለ አግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት

የሚስጠውን ትምህርት አመልካች በመሆን ጠቅሟል። ሆኖም ሥላሴ የሚለው ቃል የአግዚአብሔርን ሦስት አካልነት አንጂ አንድነቱን አያሳይም። ከዚህ የተነሣ አሐዱ-ሥሉስነት /Tri-Unity of God/ The Union of Three in One/ በሚለው ቃል ቢተካ ጥሩ አማራጭ አንደሚሆን ታምኖበታል። አስተምህሮተ ሥላሴ በግልጽ በቤተክርስቲያን ጉባኤ የተወሰነው በ381 ዓ.ም በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ነው። ውሳኔው የሚያመሰክተው አስተምህሮተ ሥላሴ የቤተክርስቲያን አቋም መግለጫ መሆኑን ነው። ዓላማውም በወቅቱ የተነሡትን የስሕተት ትምህርቶች ቤተክርስቲያን ሰመቃወም አንዲቻላት ታስቦ ነው።

3. የአስተምህሮተ ሥላሴ ጠቅለል ያለ አገላለጽ

የብዙ ሥነ መለኮት ምሁራን አስተምህሮተ ሥላሴ ስፊና ስመዝለቅ የሚያስቸግር መሆኑን ይገነዘባሉ። ሥላሴን ውስን በሆነ የሰው አውቀት ተጠቅሞ ሰማካለልና ሰመገምገም አንደማይቻል ይታወቃል። ይህን ነጥብ አስመልክቶ የሥነ መለኮት ምሁር የሆኑት ዶ/ር አንድሪው ጆን ሲናገሩ፣ «የሥላሴን ትምህርት ሰማብራራት የሚሞክር ሰው አአምሮውን ያጣል» በማለት ምን ያህል ክባድ አንደሆነ ገልጸውታል። የሥላሴ ትምህርት ከአእምሮ በላይ የሆነ ምሥጢር ነው የሚባለውም ከዚህ የተነሣ ነው። ብዙ ሰዎች የሥላሴን ትምህርት በቀላሉ ሰማስረዳት አንዲቻላቸው በዛ ያሉና የተሰያዩ ምሳሌዎችን ሰማቅረብ ሞክረዋል። ይሁን አንጂ አነዚህ ሁሉ ሰሰ ሥላሴ የተሟላ ገለጻን ሊሰጡን አይችሉም።

ይኼ ሁሉ ሆኖ ግን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ሰሰ ሥላሴ መማርና ማጥናት አንችላለን። ምክንያቱም ሥላሴ የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ ባናገኝም አስተምህሮቱ ግን በግልጽ ተጽፏልና ነው። አሁን ደግሞ ጥልቀቱና ስፋቱ በውቅያኖስ የሚመሰለውን ይህን የሥላሴ ትምህርት በአጭር በአጭሩ መዘርዘር አንጀምራለን።

ሀ. በአንዱ አምላክ ውስጥ ሦስት አካላት አሉ /እግዚአብሔር በመለኮት ባሕርዩ አንድ ነው። ነገር ግን ሦስት አካላት አሉ ሰማለት ነው/

የአስተምህሮተ ሥላሴ ትልቁ ምሥጢር «የአንድ አምላክ አንድነት ነው»። ይኸውም በአንዱ አምላክ ውስጥ ሦስት አካላት ስላሉ ነው። አነዚህም ሦስት አካላት ሦስት አምላኮች ሳይሆኑ በአንድ አምላክ ውስጥ የሚገኙ አካላት ናቸው። የሥላሴ ጥልቅ ምሥጢርም ሦስቱ አካላት በአንድ አምላክነት ብቻ ይገኛሉ የሚለው ቁልፍ አነጋገር ነው። ስለዚህ አንድ አምላክ አንጂ ሦስት አምላኮች የሉም። ከዚህ የተነሣ የአንድ አምላክ አንድነት ሁልጊዜ ምሥጢራዊነት አለው። ምሥጢሩም ቀላል ሳይሆን ሁልጊዜም ቢሆን ክባድ ነው።

በአንድ አምላክ ውስጥ የሚገኙ ሦስቱ አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። ሦስቱ አካላት እንደ ሦስት ነጠላ ስዎች የተነጣጠለ ሦስትነት የላቸውም። አንዲህ የማይሆንበት ምክንያት አንዱ የመለኮት ባሕርይ በሦስቱም አካላት ላይ በእኩል ደረጃ የሚገለጥባቸው ከመሆኑ የተነሣ ነው። ሆኖም አነዚህ ሦስቱ የግል አካልነትን ስለያዙ ግንኙነትን ሊያካሂዱ ይችላሉ። በዚህ መሠረት አብ ወልድን ይልካል፣ በወልድ በኩል መንፈስ ቅዱስንም ይልካል። ወልድ የአብን ፈቃድ ያደርጋል። ወልድ ከአብ የተቀበለውን መንፈስ ቅዱስን በሥራ ላይ ያሰማራዋል። መንፈስ ቅዱስም የአብና የወልድን ፈቃድ ይፈጽማል። የራሱንም ፈቃድ ደግሞ ያደርጋል። ይህም የፈቃዳቸውን አንድነት ያመለክታል። ይህን መለል ግንኙነታቸውም በአንድነት የሚገኙበትን ሁኔታ ይገልጻል። በመጨረሻም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አብረው በመሥራት ሂደት ውስጥ አያንዳንዱ የራሱን ሥራ ከመፈጸም አንጻር አንደሚሠራ መገንዘቡ መልካም ነው።

ሌላው ነገር በአካላት መካከል አንዱ ከሌላው የሚሰይበት የግል ባሕርይ ወይንም ጠባይ አለ። ይኸውም አብ አይወሰድም፣ ከማንም አይሰርፅም/አይወጣም። ወልድ ከአብ ከዘላለም የተወለደ ነው /ዮሐ. 1:18፣ 3:6-18፣ 1ኛ ዮሐ. 4:9/። መንፈስ ቅዱስ ከዘላለም ከአብና ከወልድ የሚሰርጽ ወይንም የሚወጣ ነው። ይህ የግል ጠባይ በአካልነቱ መካከል አንዱ ከሌላው እንደሚያንስ ወይንም እንደሚበልጥ የሚያመለክት አይደለም። ይልቁንም በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ከፍ አድርጎ የሚያንጸባርቅ ነው።

እነዚህ የሥላሴ አካላት አንድ አይነት የመለኮት ባሕርይ አላቸው። በአያንዳንዳቸውም የመለኮት ሙላት ተገልጦ የሚኖር ሲሆን፣ ሥልጣናቸውም እኩል ነው /1ቆሮ. 8:6/። ስለሆነም ወልድ ከአብ ጋር /ዮሐ. 5:21-23/፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከአብና ከወልድ ጋር /ማቴ. 12:31/ በሥልጣን እኩል መሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ የተሠመረበት ነው /ማቴ. 28:18-20/። ይሁን እንጂ አብ፣ ወልድ ወይንም መንፈስ ቅዱስ አይደለም። መንፈስ ቅዱስም፣ አብ ወይንም ወልድ አይደለም። ነገር ግን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ነው። በእስተምህሮተ ሥላሴም ትልቁ ማዕከላዊ ነጥብ የእግዚአብሔር መሰኮታዊ አንድነትና አካላዊ ሦስትነት ነው።

ለ. የሦስትነት አገላለጽ በብሉይ ኪዳን

አንዳንድ የሥነ-መለኮት ምሁራን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ሥላሴ የሚናገር ምንም ፍንጭ የለም በመሆኑም ስለ ሥላሴ ለማስተማር መነሻ የምናገኘው ከአዲስ ኪዳን ብቻ ነው ይላሉ። ይሁን እንጂ ብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ የእግዚአብሔርን አንድነት (ጥምራዊ አንድነት) የሚያሳይ ቢሆንም ሦስት አካላት እንዳሉም የሚያመለክቱ ፍንጮችንም

ይሣል። በዚሁ መሠረት ቀጥለው ያሉትን አሳቦች እንመልከት።

- በመጀመሪያ አግዚአብሔር /ኤሎሂም/ ለማያትንና ምድርን ፈጠረ /ዘፍ. 1:1/። በአማርኛ እግዚአብሔር የሚለው ቃል በዕብራይስጡ ኤሎሂም ይባላል። ይህ ስም የእግዚአብሔር ስም ሲሆን የሚያመለክተው ግን ብዙ ቁጥር ነው። በተጠቀሰው ጥቅስ ውስጥ ያለው ግሥ ግን ነጠላ ነው። ኤሎሂም የሚለው የብዙ ቁጥር ከነጠላ ግሥ ጋር መጣመሩ በአንድነት ውስጥ ብዙ ቁጥር እንዳለ ይጠቁመናል። ይህም ብዙ ቁጥር ሥላሴን አመልካች ነው።

- እግዚአብሔር /ኤሎሂም/ ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ /ዘፍ. 1:26/። «እንሥራ» የሚለው ግሥ የብዙ ቁጥርን ያመለክታል። ስለሆነም ሥላሴን ጠቋሚ ግሥ ነው።

- ከዚያም እግዚአብሔር አምላክ /ያህዌ፣ ኤሎሂም/ ሰው መልካምና ክፋውን ለይቶ በማወቅ ረገድ አሁን ከእኛ እንደ አንዱ ሆኖአል /ዘፍ. 3:22/። እኛ የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር አመልካች ነው። ስለዚህ ከሥላሴ ጋር የተያያዘ መሆኑን ያስገነዝበናል።

- ኑ እንውረድ፣ እርስ በርሳቸውም እንዳይግባቡ ቋንቋቸውን እንደበላልቀው /ዘፍ. 11:7/፣ «ኑ እንውረድ» የብዙ ቁጥር ነው። ከሁለት በላይ የሆኑ ቁጥሮችን አመልካች ነው። ስለሆነም የሥላሴን ጉዳይ የሚጠቁም ነው። እዚህ ላይ ከሁለት የሚበልጥ ቁጥር ሁሉ ጸሎት ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን በሙላት ከተገለጠው የሥላሴ ፅንሰ አሳብ ሳቢያ እነዚህ ጥቅሶች ስለ

እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ይናገራሉ ማለት ይቻላል።

- ቀትር ላይ አብርሃም በመምሬ ትልልቅ ዛፎች አቅራቢያ በምትገኘው ድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር /ያህዌ/ ተገለጠለት፤ ቀና ብሎም ሲመለከት፣ ሦስት ሰዎች ቆመው አየ፣ ወዲያውም ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ፈጥኖ ወደ ሰዎቹ ሄደ፣ ወደ መሬት ዝቅ ብሎም አጅ ነሣ ... ሰዎቹም ሰመሄድ ሊነሱ፣ ቁልቁል ወደ ሰዶም ተመለከቱ፣ አብርሃምም ሊሸኛቸው አብሮአቸው ወጣ /ዘፍ. 18:1-3,16/። እዚህ ላይ አብርሃም ያየው አንድ አምላካዊ አካልና ሁለት መላእክት እንደሆኑ የሚያመለክት ሁኔታ ነው። በዚህ ክፍል አገላለጽ በእግዚአብሔር የጥምር አንድነት ከአንድ በላይ የሆኑ አካላት እንዳሉ ይጠቁመናል። ይህም ሥላሴን ሊያመለክት ይችላል።

- ከዚያም እግዚአብሔር /ያህዌ/ በሰዶምና በገሞራ ላይ ከሰማይ ከእግዚአብሔር /ያህዌ/ ዘንድ የሚቃጠል ዲንና እሳት አዘነበባቸው /ዘፍ. 19:24/። ከዚህ ክፍል ደግሞ ሁለት የተለያዩ አካላት እግዚአብሔር ተብለው እንደተጠሩ ልንመለከት እንችላለን። ሥላሴን አመልካች መሆኑንም ከዚህ ግንዛቤን ማግኘት ይቻላል።

- ኤሎሂም የሚለው የዕብራይስጥ ቃል የእግዚአብሔር ስም ማለት እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተነዋል። ይህ ስም ደግሞ ለሁለት የተለያዩ አካላት መሰጠቱን ከመዝ. 45:6-7 ላይ መመልከት እንችላለን። ይህም ከሥላሴ ጋር የተያያዘ ነው።

- በኢሳ. 6:3 እና በራእይ 4:8 ላይ ሦስት ጊዜ የተደጋገመው የእግዚአብሔር ቅድስና ለእያንዳንዱ አካል የተሰጠ ሊሆን

ይችላል። በዚህ መልክ ሦስት ጊዜ መደጋገሙ ሥላሴን ከማመልከት አንጻር ነው ብለን ልናስብ አንችላለን።

- ብሉይ ኪዳንን ስናነብ የእግዚአብሔር ወይንም የጌታ መልአክ የሚል ሐረግ ተጽፎ እናገኘዋለን። በዚህ አገላለጽ የተገለጸው መልአክ ተግባሩን በምናጤንበት ጊዜ ከመለኮት አካላት አንዱ እንደሆነ ወይንም

እግዚአብሔር መሆኑን ያስገነዝበናል። ይህ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር መላኩንና ነገር ግን ከላኪው ከእግዚአብሔር ደግሞ የተለየ መሆኑንም ያመላክተናል። ለዚህ ማስረጃችን ይሆኑ ዘንድ በዘፍ. 16:7-14 ለአጋር፣ በዘፍ. 22:11-18 ለአብርሃም፣ በዘፍ. 31:11-13 ለያዕቆብ፣ በዘጸ. 3:25 ለሙሴ፣ በዘጸ. 14:19 ለእሥራኤል፣ በዘዳ. 22:22-35 ለበለአም፣ በመሳ. 6:11-23 ለጌዴዎን፣ በመሳ. 13:2-25 ለማኑሄ፣ በ1ኛ ነገ. 19:5-7 ለኤልያስ፣ በ1ኛ ዜና. 21:15-17 ለዳዊት እንደተገለጠ፣ በ2ነገ. 19:35 /185000 አሥራውያንን እንደገደለ፣ በዘካ. 3:1 ኢያሱን ከሰይጣን ክስ እንደታደገው ጥቀስ እንችላለን።

ከላይ እንደማስረጃ ከጠቀስናቸው ክፍሎች የምንረዳው ከሥላሴ አካላት አንዱ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ መልክ ይገለጥ እንደነበርና ወደፊት ደግሞ ሥጋ ለብሶ እንደሚመጣ የሚያመለክተውን የብሉይ ኪዳን ጥላነትን ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሥላሴን ትምህርት በማያሻማ መልኩ ማግኘት ባንችልም፣ በአዲስ ኪዳን መነጽር ስንመለከተው ግን ለስተምሀርቱ በሚገባ በውስጡ ተካቶና ተገልጸ ይገኛል። ሁልጊዜም ቢሆን ብሉይ ኪዳንን በአዲስ ኪዳን ብርሃን መመልከት አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ስለሆነና ብሉይ ኪዳን ደግሞ በአዲስ ኪዳን ድምዳሜ ወይንም መልስ ያገኘበት በመሆኑ ነው።

ሐ. የሥስትነት አገላለጽ በአዲስ ኪዳን

ስማያሻማ ሁኔታ አስተምህሮተ ሥላሴ የተገለጸው በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ነው። ምክንያቱም ቃል የሆነው እግዚአብሔር ሥጋ ስለገለበጡ /ዮሐ. 1:14/ እግዚአብሔር የሆነው መንፈስ ቅዱስ ስለመውረዱና /ኢዩ. 2:28፣ የሐዋ. 2:1-4፣ እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር አብ ፈቃዱን በወልድና /ዮሐ. 4:34/ በመንፈስ ቅዱስ /የሉቃ. 1:35፣ ሮሜ. 8:27/ መፈጸሙን አጉልቶ በማሳየቱ ነው።

አዲስ ኪዳን አስተምህሮተ ሥላሴን በግልጽ አስተዋውቋል። በብሉይ ኪዳን ጎልቶ በሚታወቀው በእግዚአብሔር የጥምር አንድነት ውስጥ ሦስት መለኮታዊ አካላት እንዳሉም በግልጽ ያስቀምጣል። ሦስቱም አካላት ደግሞ ግልጽ በሆነ ሁኔታ እግዚአብሔር መሆናቸውን ያረጋግጣል። አዲስ ኪዳንን በምናስስበት ጊዜ ይህን እውነት በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ተገልጾ እናገኘዋለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአገልግሎቱ ፍጻሜ ላይ አሕዛብ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲጠመቁ በማዘዝ የእግዚአብሔርን አንድነትና የአካል ሦስትነት ስሚገባ ገለጠ /ማቴ. 28:19-20/። ስም የሚለውን ነጠላ ቃል በመጠቀምም ሦስቱ አካላት አምላኮች እንዳልሆኑ አረጋገጠ። ስለሆነም እነዚህ ሦስቱ አካላት በመለኮትና በባሕርይ አንድ ሆነው በአንድ አምላክ ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

በሠላሳ ዓመቱ ወልድ በሚጠመቅበት ጊዜ አብ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስ በአካል መልክ እንደ እርግብ በክርስቶስ ላይ ተቀምጧል። ከዚህም ሦስቱን የሥላሴ አካላት በግልጽ ማየት እንችላለን /ማቴ. 3:16-17፣ ማቴ. 1:10-11፣ ሉቃ. 3:22/።

ይህ ብቻ ሳይሆን ስውን በማዳን ሥራ የየግላቸው የግብር ድርሻ እንዳላቸውና ነገር ግን ዓላማቸውና ፈቃዳቸው አንድ እንደሆነ ቀጥሎው ከተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ግንዛቤን ማግኘት ይቻላል /ማቴ. 3:16-17፣ ማር. 1:10-11፣ ሉቃ. 3:22፣ ዮሐ. 1:32/። እነዚህ ጥቅሶች የመለኮት አካላት በአንድነት መገለጻቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ማቴዎስና ሉቃስም የኢየሱስ ክርስቶስን ታሪክና ትምህርት በሚጽፉበት ጊዜ እነዚህን ሦስት አካላት በጽሑፋቸው ውስጥ በመጥቀስ ይታወቃሉ /ማቴ. 12:28፣ ሉቃ. 1:35፣ 4:17-19፣ 10:21፣ 24:48/። ከዚህ የምንረዳው በወልድ የጥምቀት ሥርዓት የተገለጸው ሥላሴ ጽኑ የሆነ የእምነታቸው መሠረት መሆኑን ነው።

ሌላው የሥስትነት አገላለጽ በግብራቸው በኩል የተንጸባረቀው ነው /Economic Trinity/። ይህን መስል አገላለጽ የምናገኘው በአዲስ ኪዳን መልእክቶች ውስጥ ነው። ሐዋርያ ጳውሎስ ይህን ግብራዊ ሦስትነት አንዲህ ይገልጠዋል የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ሕብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን /2ኛ ቆሮ. 13:14/። ሐዋርያው ጳውሎስ አያንዳንዱን አካል ከግብሩ ጋር አያይዞ በመግለጥ ግብራዊ/ምግባራዊ ሦስትነትን ግልጽ አድርጓል። ከዚህ አገላለጽም ሦስቱን አካላት በግልጽ መመልከት እንችላለን።

እነዚህ አካላት ተለዋጭ ስሞች ስላሉዋቸው ቋሚ በሆነ መጠሪያ ስሞች ላይጠሩ ይችላሉ። ጳውሎስ እዚህ ላይ እግዚአብሔር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መንፈስ ቅዱስ ይበል እንጂ በሌላ ጊዜ ግን እግዚአብሔርን «አብ» /ኤፌ. 3:14/፣ ኢየሱስ ክርስቶስን «ወልድ» /ገላ. 4:4/፣ መንፈስ ቅዱስን «መንፈስ» /ኤፌ. 3:16/ በማለት በምትክ ስሞች በመጠቀም ገልጿል። በአጠቃላይ ጳውሎስ በተደጋጋሚ በሚጽፋቸው ደብዳቤዎች ውስጥ ሦስቴን አካላት በሚገባ ገልጿል /ሮሜ. 8፣ 15:15- 16፣

15:30፣ 1ኛ ቆሮ. 12:4-6፣ 2ኛ ቆሮ. 1:21-22፣ 3:3፣ 13:14፣ ገላ. 4:4- 6፣ ኤፌ. 1:3-14፣ 2:18፣ 3:14-17፣ 4:4-6፣ ፊል. 3:3፣ 2ኛ ተስ. 2:13- 14/::

እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥበት መንገድ በሥራ ነው:: ይህ የሦስቱም አካላት ባሕርይ ስለሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከግብር ጋር ተያይዘው ተገልጠዋል:: አኖም ያወቅናቸው በግብራቸው ነው:: ጌታችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስም እነዚህን ሦስቱን አካላት የጠቀሰው በጥምቀተ መነሻነት ነበር /ማቴ. 28:19-10/:: ስውን በማዳን አፈጻጸም የአካላቱ ድርሻ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ስፍራዎች ተጽፎ እንዳለ አናውቃለን:: ይሁን እንጂ ስዚህ ዓለማ ላይ የሁሱም ፈቃድ አንድ ዓይነት ነው:: ስለሆነም የሦስቱም ተግባራዊ ድርሻዎች በአንድ ፈቃድ ውስጥ የተካተቱ ናቸው:: የጋራ ዓላማቸውንም ከግቡ ለማድረስ ግብራቸው እርስበርስ የተሳሰረና የተቀናጀም ነው::

የሥላሴ አካላትን ግብር በሚመለከት የእያንዳንዳቸውን ድርሻ ቀጥሎ ባለው መልክ ማስቀመጥ እንችላለን::

- እግዚአብሔር አብ፡ የሚወስን፣ የሚያረጋግጥ፣ የሚፈርድና የሚሾም አካል ነው::
- እግዚአብሔር ወልድ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መድኃኒት፣ አዳኝ፣ የአማኞች ዋስትና፣ ታላቁ ሊቀ ካህናትና እርሱን ይመስሉ ዘንድ ዳግም የሚፈጠሩበት አካል ነው::
- መንፈስ ቅዱስ የምእመናንን ሕይወት እስከ ጌታ ዳግም ምጽአት ድረስ በቀጣይነት የሚቀድስ፣ ኃይልን በመስጠት ስለገልግሎት ብቃትን የሚያላብስ፣ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራና የምእመናን ርስት ዋስትና የሚሆን አካል ነው::

ሐዋርያው ጴጥሮስም የሥላሴ አካላትን ምግባራዊ ሦስትነት /Economic Trinity/ በስብከቱ ወቅት ገልጿል:: «ስስዚህ /ኢየሱስ/ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ካለ በኋላ፣ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከአብ ተቀብሎ አሁን የምታዩትንና የምትስሙትን አፈሰሰው» /የሐዋ. 2:33/ በማለት በመንፈስ ቅዱስ አስጣጥ ላይ የአብንና የወልድን ሥራ ሲገልጥ እንመሰክታለን:: መጀመሪያ በጻፈው መልእክቱ ላይም ከግብራቸው ጋር በማያያዝ የመሰከት አካላትን በሚገባ አንፀባርቋል:: እንዲህ በማለት «እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ ያወቃቸው፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ስመታዘዝ በደሙ ስተረጨትና ስመንፈስ ለማካይነት ስተቀደሱት፣ ጸጋና ስላም ይብዛላችሁ» /1ኛ ጴጥ. 1:1-2/ እያለ የአብን አስቀድሞ መወሰንን፣ የወልድን ደም መርጨትና የመንፈስ ቅዱስን መቀደስ ያብራራል::

በመቀጠልም ይሁዳ የሦስቱን አካላት ተግባር ከአማኞች ጋር በማያያዝ እንዲህ በማለት ይገልጻል:- «እናንተ ግን ... በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያደርሳችሁን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረት ስትጠባበቁ ሳስ ስእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ» /ይሁዳ. 20-21/ እያለ የሦስቱ አካላት ተግባር በአንድ አማኝ ሕይወት ውስጥ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያመላክታል:: ከዚሁ ጋር አያይዞ ምግባራዊ ሦስትነትንም ሸግልጽ እንዳሰየ መመልከት እንችላለን::

ሐዋርያ ዮሐንስም በጻፋቸው መጻሕፍት ምግባራዊ ሦስትነትን አስመልክቶ የሥላሴ አካላትን ሰሚገባ ገልጿል:: በጻፈው ወንጌል ሰዎች ኢየሱስን በእግዚአብሔር ልጅነቱ እንዲያምኑና የዘላለም ሕይወት ባለቤት እንዲሆኑ ዘግቧል /ዮሐ. 20:31/:: ከዚህ ጋር አያይዞም ኢየሱስ ከአብ ዘንድ መምጣቱን፣ ከእርሱም ጋር አንድ መሆኑንና ሥራውም በመንፈስ ቅዱስ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ግልጽ አድርጓል::

በጌታችንና በኒቆዲሞስ መካከል በተደረገው ንግግር ውስጥም ዮሐንስ የሦስቱን ሥላሴ አካላት በጽሑፍ መጥቀሱን እናውቃለን። ከዚህ በላይ ግን ከምዕራፍ 14-16 ባለው ክፍል የአካላቱን ምግባራዊ ሦስትነት ግልጽ በሆነ ሁኔታ በእንድነት ጠቅሷቸዋል፦

> እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም የእውነት መንፈስ ነው /ዮሐ. 14:16-17/።
>
> አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያስታውሳችኋል /ዮሐ. 14:26/።
>
> እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሚወጣው አጽናኙ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ በስለ እኔ ይመሰክራል /ዮሐ. 15:26/።
>
> እኔ ካልሄድኩ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣም፤ ከሄድሁ ግን እርሱን ወደ እናንተ እልክለሁ፤ በሚመጣበትም ጊዜ ዓለምን ስለ ኃጢአት፤ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል። ስለ ኃጢአት ሊባል፤ ስለ ጽድቅ፤ ወደ አብ ስለምሄድና ከአሁን ስለማታዩኝ ነው /ዮሐ. 16:7-10/።
>
> አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ ... መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ... አላቸው /ዮሐ. 20:21-23/።

ሐዋርያው ዮሐንስ በጻፈው ራእይም የሥላሴ አካላትን በልዩ ልዩ አጠራርና ምሳሌ በአንድነት ጠቅሷቸዋል። ስምሳሌ

በምዕራፍ አንድ መግቢያ ላይ የሚገኘው የዮሐንስ ገላጭ ጽሑፍ የራእዩ መሠረት በሥላሴያዊ ዓውድ ላይ የሚያተኩር መሆኑን የሚያመላክት ነው /ራእይ 1:4-6/። ስለሆነም የተጠቀሰውን ክፍል ረጋ ብለን ብናስስ ሦስቱም አካላት እንዳሉ ማረጋገጥ እንችላለን።

አስከአሁን ያየነው የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አብዛኛውን ጊዜ የሥላሴ አካላትን አንድ ላይ በማድረግ መግለጻቸውን ነው። አልፎ አልፎ ግን ከሦስቱ አካላት ሁለቱን ወይንም አንዱን ብቻ የጠቀሱበትም ጊዜ እንደነበር ይታወቃል። ይሁን እንጂ አስባቸው ሲመረመር ከጀርባቸው ሦስቱም አካላት እንዳሉ አመልካች ነው። ከዚህ የምንረዳው ምሥጢረ ሥላሴ የትምህርታቸው መሠረትና ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ነው።

ምዕራፍ ስድስት

አስተምህሮተ ሥላሴ /Doctrine of Trinity/

1. የአካል ትርጉም

አካል ከሰው ጋር በተያያዘ መልኩ ሲገለጥ መሳው የሰውነት ብልቶችን የሚያጠቃልል ማለት እንደሆነ ይገባናል። ሌላው አመለካከት ደግሞ የሰው አካልነት ማለት ሲያሰብ የሚችል፣ ስሜትና የመፍቀድ ችሎታም ያለው ነው የሚል ነው። ይህ እውነተኝነት ያለው አመለካከት ነው። ስለሆነም ሰው አስቦ እንዲሠራ ተደርጎ የተፈጠረ ነው። ሲነካ ደግሞ መነካቱን የሚገልጥበት ስሜት አለው። በግብረገብ አንጻርም በሁለት ነገሮች መካከል የመምረጥ ነፃ ፈቃድ ያለው ፍጡርም ነው።

ሰው በእግዚአብሔር መልክ ይፈጠር እንጂ አካሉ ከፈጠረው ፈጣሪ አካል ጋር አንድ አይነት አይደለም። ይሁን እንጂ በሁለቱ መካከል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የመመሳሰል ሁኔታ አለ። በዚሁ መሠረት አግዚአብሔር እውቀት እንዳለው ሁሉ ሰውም ደግሞ እውቀት አለው። ልዩነቱ የአግዚአብሔር እውቀት ገደብ የሌለው፣ ፍጹምና ምልአት ያለው ሲሆን፣ የሰው ግን የተገደበ ነው። የእግዚአብሔርም እውቀት ከሰው እውቀት የዘለለምን ያህል ይበልጣል።

ሌላው እግዚአብሔር ፍቃድ እንዳለው ሁሉ ሰውም ደግሞ የራሱ የሆነ ፍቃድ አለው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍቃድ በራሱ የቆመና በምንም ሳይ ያልተደገፈ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ እንደ ፍቃዱ የማድረግ ሙሉ ሥልጣን አለው። የሚከለከለውና የሚያግደው ነገር የለም /ኢዮ. 42:2/። የሰው ፈቃድ በሁለት ነገሮች መካከል መምረጥን መሠረት ያደረገ በሰሆነ የተገደበና ተጠያቂነትም ያለበት ነው /ዘፍ. 2:16-17/።

በሦስተኛ ደረጃ አግዚአብሔር ሰሜት እንዳለው ሁሉ ሰውም እንዲሁ ሰሜት አለው። ልዩነቱ ሰው ሲበድል በሰሜቱ ለኃዘን ይጋለጥ ይሆናል። አግዚአብሔር ግን ፃድቅ ስለሆነና ሰለማይላላት ሰሜቱ የበደል መግለጫ አይደለም። አይሆንምም። እርሱ ፍጹምና ሁሉንም ነገር በአምላካዊ እውቀቱ የሚያደርግ ነውና። ሰው ግን ኃጢአተኛ ከመሆኑ የተነሣ አካሉ በከፋት አሳብ፣ በፍርሃት፣ በክንቱ አስተሳሰብና በመላለሱት የተከበበ ነው። በስዚህ ሰሜቱ የበደልና የጉድለት መግለጫ ነው።

ሌላው አስተሳሰብ ደግሞ ሰው አካላዊነቱን የሚያሳየው በአካሄዱ ከሌሎች በመለየት፣ ሰሌሎች ሥራ በመሥራት፣ ከሌሎች ጋር ግንኙነት በማድረግና አመክንዮአዊ አስተሳሰቡን በመግለጥ ነው የሚል ነው። እነዚህ መለኪያዎች ለመላእክትም ጭምር የሚሠሩ ናቸው። እነርሱም አካል ያላቸው ፍጡራን ናቸውና። ማወቅ ያስብን እግዚአብሔር አካል ያለው አምላክ ስለሆነ የአካልነት መሠረቱ ሌላ ሳይሆን እርሱ መሆኑን ነው። ከዚህ የተነሣ አካልነቱ ከሰውና ከመላእክትም እጅግ የላቀ ነው። ሰው ከሌሎች ጋር የሚኖረውን የኑሮ ዘይቤ ማለትም ሰሌሎች የመሥራትን፣ ከሌሎች ጋር የሚገናኝበትን መንገድና አሳቡን የሚገልጥበትን አቅጣጫ ከማሰብ ተነሥተን የእግዚአብሔርን አካላዊነት የቱን ያህል እንደተረዳን መገመት እንችላለን።

አስከአሁን ድረስ ሦስቱ አካላት በአንድ አምላክ ብቻ ይገኛሉ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃን መሠረት በማድረግ ተመልከተናል። ጨምረንም የምግባር ድርሻቸውን፣ የተቀናጀና የተሳሰረ ግኙነታቸውንም ዳሰናል። ከግንኙነት አንጻር ወልድ የአብ ልጅ መሆኑንና በመካከላቸው ደግሞ ሰው ማሰብ ከሚችለው በላይ የሆነ አስደናቂ ፍቅር እንዳለ የታወቀ ነው። እነዚህ በአንድ አምላክ ውስጥ የሚገኙ ሦስት አካላት ከመለኮታዊ ባሕሪያቸው የተነሣ ከሰው ይልቅ የእነርሱ አሳብ፣ ዕቅድ፣ ዓላማ፣ ፈቃድና ሰሜት እጅግ የላቁ ናቸው። አካልነታቸውም ደግሞ ፍጹምና ምሉዕ ነው።

ሰው ግን ከኃጢአት የተነሣ በአካሉ ግድፈትና ጉድለት አለበት። ከዚህ ስመነሣትም ፍጡር ከሆነው ሰው ይልቅ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ አካላዊ እንደሆነ መረዳት እንችላለን።

ከሰዎችና ከመላእክት አንፃር ስናይ እያንዳንዱ ሰው ወይንም መልአክ የራሱ የሆነ አካልና ህላዌ /መኖር፣ መሠረት፣ አቋም.../ አለው። ከእግዚአብሔር አኳያ ግን ህላዌ /መኖር፣ መሠረት፣ አቋም .../ አንድ ብቻ ነው። ሦስቱም አካላት የየራሳቸው ህላዌ ቢኖራቸውም የሦስቱም አካላት ህላዌ ግን ያው የአንዱ እግዚአብሔር ህላዌ ነው። ጥያቄ ቢነሣ ምስጢር ነው ከማለት ሌላ አማራጭ የለም። በተመላላይ መልኩ የሦስቱ የእያንዳንዳቸው መለኮትነት ያው የአንዱ እግዚአብሔር መለኮት ነው። ባሕርይም ቢሆን የእያንዳንዳቸው ባሕርይ የአንዱ እግዚአብሔር ባሕርይ ነው። ስለሆነም የሦስቱ አካላት የባሕርይ መገለጫዎች ያው የአንዱ እግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫዎች ናቸው። እግዚአብሔር በመለኮትና በባሕርይ አንድ ነው የሚለው የሥላሴ ማዕከላዊ ትምህርት መሠረቱ ይኼ ስለሆነ ትምህርቱን ከመቅሰሙ አኳያ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል።

2. የአንድነት ትርጉም

እዚህ የምናነሣው አንድነት አንድ፣ ሁለት፣ ብለን የምንቆጥረውን የተፈጥሮ አቆጣጠር ስሌትን አይደለም። ይህ ከሆነማ የሒሳብ እንድነት መሆኑ ነው። ማሳሰቢያው እንዲህ ዓይነቱን የእለምሮ ስሌት መሠረት በማድረግ ይህን ክፍል ለመመልከት እንዳንሞክር ለማለት ነው። በመሠረቱ ቀጥለን የምንመለከተው እንድነት ምሥጢራዊ አንድነት ነው። ስለሆነም በአእምሮ ስሌት የሚደረስበት አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ እኔና አብ አንድ ነን /ዮሐ. 10:30/ ሲል እኛ የምናውቀውና ከሒሳብ ስሌት የተገኘ «አንድ» ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል። ኢየሱስ የተናገረው ዓይነቱ «አንድነት» ግን ከአእምሮአችን በላይ የሆነና ምሥጢራዊ የሆነ እንድነት ነው።

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ የምናገኘው የባልና የሚስት «አንድ ሥጋ» መሆን ነው /ዘፍ. 2:24/። የዚህ ዓይነትም አንድነት ምሥጢር ነው /ኤፌ. 5:31-32/ ተብሎ ተጽፎአል። መረዳት የሚገባን ትልቁ ነገር የሥላሴ አንድነት በሒሳብ ስሌት የተቀመረ ላይሆን፣ ከአእምሮ በላይ የሆነ ምሥጢራዊ አንድነት ነው። ይህን ምስጢር በብቃት ሲገልጥ የሚችል ምሳሌንም ማግኘት ያስቸግራል።

ብዙ ጊዜ እንቁላል ሲጠቀስ እንሰማለን። የአንድ እቁላል ሶስቱን ክፍል /ቅርፊቱ፣ አስኳሉና ውኃውን/ በመውሰድ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ለማብራራት ሙከራ ሲደረግ ይታያል። የአንድ እንቁላል ክፍሎች ሦስት ይሁኑ እንጂ አንድ ዓይነት ህላዌ /መኖር፣ መሠረት፣ አቋም.../ የላቸውም። ነገር ግን የሥላሴ አካላት ሦስት ይሁኑ እንጂ ህላዌያቸው አንድ ነው። ስለዚህ የእንቁላል ምሳሌነት የሥላሴን ምሥጢር ለመግለጥ ጉልበት የለውም። ደግሞም አምላካችን የሰማያትና የምድር ሁሉ ፈጣሪ /ዘፍ. 1:1/ የሆነ ዘላለማዊ አምላክ እንጂ /ዕብ. 1:10-12/ እንቁላል አይደለም።

3. የሥላሴ ምሥጢር

ሥላሴ ምሥጢር ነው። ምሥጢርነቱም ከሰው አእምሮ በላይና የማስተዋል ኃይልም የማያቋርጠው ሠፊ ውቅያኖስ ነው። በአካላት መካከል ካለው ግንኙነት በመነሣት አንዳንድ ነገሮችን መረዳት እንችል ይሆናል። የህላዌያቸውን አንድነት ግን ለማስብ አቅም ያንሰናል። ይሁን እንጂ ፈላስፎች ፍልስፍናቸውን መሠረት በማድረግ ብዙ ጥረት እንዳደረጉ ይታመናል። ውጤቱ ግን የስሕተት አሠራሮች የተመረቱበት ሆነ። አሰቸጋሪውና ተፈታታኙ ነገር የእያንዳንዱን የሥላሴ አካል ህላዌ ከሌላው ጋር እንዴት ሲገናኝ እንደሚችል ማለየቱ ላይ ነው። የሥነ መለኮት ጥናትም ቢሆን ይህን ምሥጢር ሊፈታ አይችልም። ከዚህ አንጻር የትምህርታችን ዓለማ በተገለጠው ላይ በማተኮር ላይገለጥ የቀረው

ደግሞ ምን እንደሆነና ምሥጢሩ እምን ላይ እንዳለ አገልጋዮችና ምእመናን ወደ መረዳት እንዲመጡ ማስቻል ነው።

4. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሥላሴ ትምህርት በሦስት ዓረፍተ ነገሮች ሲጠቃለል

ሀ. እግዚአብሔር ሦስት አካላት ነው

1. በሦስቱ አካላት መካከል ልዩነት አለ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር አብ ፊት ስለ እኛ ይማልዳል /1ዮሐ. 2:1፣ ዕብ. 7:25/። ይህ የኢየሱስ አገልግሎት አርሱ ከአብ ልዩነት ያለው አካል መሆኑን ያመላክታል።

አንዲሁም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ስለ እኛ ይጸልያል ወይንም ይማልዳል /ሮሜ. 8:27/። መንፈስ ቅዱስም ደግሞ አንዲህ ለመጸለይና ለመማለድ ከአብ የተለየ አካል ያለው መሆን ይናርበታል።

በዮሐንስ ወንጌ ቅዱስ ል ምዕራፍ 16 ቁጥር 7 ላይ ደግሞ በኢየሱስና በመንፈስ መካከል ልዩነት አንዳለ በግልጽ ማየት አንችላለን።

2. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ /The Trishagion : Holy, Holy, Holy/

በትንቢተ ኢሳይያስ 6:3 ላይ ለሦስት ጊዜ ያህል መላእክቱ ቅዱስ ማለታቸው ሦስቱን አካላት የሚያመላክት ሊሆን ይችላል።

ለ. እያንዳንዱ አካል ሙሉ እግዚአብሔር ነው

1. የአብ መለኮትነት /The Deity of the Father/

በመጀመሪያ አግዚአብሔር /Elohim/ ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ /ዘፍ. 1:1/። ኤሎሂም የሚለው የዕብራይስጡ ብዙ ቁጥር የሥላሴን አካላት የሚያመለክት ስለሆነና አብም በውስጡ የተጠቃለለ ስለሚሆን የፈጣሪነቱ ተግባር መለኮታዊነቱን ወይንም አግዚአብሔነቱን ይገልጣል። ቀጥለው ያሉትም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች «አግዚአብሔር» ወይንም መለኮት መሆኑን የሚያላዩ ናቸው /ማቴ. 6:26-30፣ ዮሐ. 6:27፣ ሮሜ. 1:7፣ 1ኛ ቆሮ. 8:4-6፣ ገላ. 1:1/።

2. የወልድ መለኮትነት

ቀጥለው ያሉትን ጥቅሶች በማንበብ የወልድን መለኮትነት መረዳት አንችላለን።

በመጀመያ ቃል ነበረ፣ ቃልም ከአግዚአብሔር ጋር ነበረ /ዮሐ. 1:1/።

ቶማስም ጌታዬ አምላኬም አለው /ዮሐ. 20:28/።

የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በርሱ ይኖራልና /ቆላ. 2:9/።

ስለ ልጁ ግን እንዲህ ይላል፣ አምላክ ሆይ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ጸንቶ ይኖራል፣ ጽድቅም የመንግሥትህ በትር ይሆናል /ዕብ. 1:8፣ የማር. 2:8-18/ በተጨማሪ ተመልከት/።

3. የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት

ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለ፣ «ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ስይጣን ልብህን ለምን ሞላው? ...የዋሸኸው አኮ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም» /የሐዋ. 5:3-4/። ክፍሉ በግልጥ የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነትን የሚያሳይ ነው። ቀጥሰው ያሱትም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነትን የሚያመለክቱ ናቸው። /ማቴ. 28:19፣ 1ኛ ቆሮ. 2:10-11፣ መዝ. 139:7-10፣ ዘካ. 4:6/

ሐ. እግዚአብሔር ያልተከፋፈለ አንድ አምላክ ነው

ብዙ ጣአታት በሚመለኩበት ዘመን ሙሴ ለኪዳኑ ሕዝብ እግዚአብሔር አንድ መሆኑን በማስመልከት እንዲህ አለ፤ «እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው» /ዘዳ. 6:4/ በማለት ያረጋግጥላቸዋል። ከዚህ አንጻር በዕብራይስጥ ቋንቋ አንድነትን ለማመልከት ሁለት ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል። እነርሱም

1/ ኤካድ

- የጥምረትን አንድነት የሚያመለክት ቃል ነው /ዘፍ. 2:24/።
- የእግዚአብሔር አንድነትም የጥምረት አንድነት ነው /ኢሳ. 45:4-6፣ 21-22፣ 44:68፣ 1ኛ ጢሞ. 2:5፣ 1ኛ ቆሮ. 8:6፣ ሮሜ. 3:30፣ ያዕ. 2:30/።

2/ ያቻድ

አሃዳዊ እንድነትን የሚያመለክት ቃል ነው።

ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት እንዲኖረን ይህን መሠረታዊ የሆነ ትምህርተ ሥላሴን /እግዚአብሔር ሦስት አካላት ነው። እያንዳንዱ አካላት መሉ እግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር ያልተከፋፈለ አንድ አምላክ ነው/ አምኖ መቀበል የግድ ይላል።

5. ስለተምሀሮተ ሥላሴን በመካድ የተነሡ የስሕተት ትምህርቶች (Heresies that Deny the Doctine of Trinity)

ከቤተክርስቲያን የታሪክ ሂደት እንደምንረዳው፣ ከላይ ከተመለከትናቸው ሦስት መሠረታዊ የትምህርተ ሥላሴ እውነቶች መካከል ቢያንስ አንደኛውን በመካድ ወይንም በመቃወም የተነሡ ስለተምህርተ ሥላሴን የሚጻረሩ ትምህርቶች አሉ። ከእነዚህ የስሕተት ትምህርቶች መካከል ሰባቱን እንመለከታለን።

ሀ/ ኢየሱስ ብቻ /ሞዳሊዝም (Jesus only or Modalism)

ይህ የስሕተት ትምህርት የሚሰው እግዚአብሔር ሦስት አካላት ሳይሆን አንድ አካል ነው። ይህ አንድ አካል የሆነው እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ስልቶችና (Modes) ቅርጾች /forms/ ራሱን በመሰዋወጥ ይታያል በማለት ያስተምራል። በሌላ አባባል አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን የነበረው እግዚአብሔር አብ በአዲስ ኪዳን አብ መሆኑን በማቆም ወልድ ወደ መሆን መጣ። ወልድ ካረገ በኋላ ደግሞ ወልድ መሆኑ ቀርቶ መንፈስ ቅዱስ ሆኖ መጣ የሚል ትምህርት ነው። ይህን በምሳሌ ሲያስደግፍ፣ በረዶ ሲቀልጥ ውኃ ወደ መሆን ይለወጣል። ውኃ ሲፈላ ደግሞ ወደ እንፋሎትነት ይለወጣል። እነዚህ ሦስቱ የጠጣርነት፣ የፈሳሽነትና የእንፋሎትነት ቅርጾች የውኃ መገለጫዎች እንደሆኑ ሁሉ፣ አንድ አካል የሆነውም እግዚአብሔር ራሱን በሦስት አይነት መንገድ በመቀያየር ተገልጧል ብሎ በማስተማር ስለተምህርተ ሥላሴን ይጻረራል።

የዚህ ትምህርት ጀማሪ "sabellius" የሚባል የስሕተት መምህር ነበር። ከዚህ የተነሣ ትምህርቱም "sabellianism" ተባለ። ጊዜው በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነበር። በአገራችን ተከታዮች ያሉት ሲሆን ዛሬ የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ተከታዮች በመባል የሚታወቁ ናቸው። ይህ የሐሰት ትምህርት ሦስቱ አካላት በአንድነት ሆነው የተገለጡበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አውነትን በመቋቋም ማስረጃ የማቅረብ ብቃትና ጉልበት የለውም።

ለ/ አርዮሳውያን (Arianism)

የስሕተት ትምህርቱ አፍላቂ አርዮስ የሚባል የአሌክሳንድርያ ቄስ ነበር። ጊዜው በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን ትምህርቱም በስሙ ሊሰየም ችሏል። የዚህ ትምህርት ዋነኛው ነጥብ እግዚአብሔር ወልድ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ የተፈጠረ ፍጡር ነው። እግዚአብሔር ወልድ ከሁሉ ፍጥረታት ይበልጣል። ቢሆንም ከእግዚአብሔር አብ ግን የሚያንስ ፍጡር ነው የሚል ነው። ደግሞም ኢየሱስን ከአብ ሊያስተካክሉት የሚችሉ ባሕሪያት የሉትም ይላል። ኢየሱስ ፍጡር መሆኑንም ለማመልከት ቀጥሎው ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማስረጃነት ይጠቅሳል። /ዮሐ. 1:14; 3:16, 18፤ 1ኛ ዮሐ. 4:9፤ ቆላ. 1:15፤ በተጨማሪም ምሳ. 8:22 ይጠቅሳል/።

በአገራችን የዚህ እምነት ተከታዮች ራሳቸውን «የይሖዋ ምሥክሮች» (Jehovah's Witnesses) ብለው የሚጠሩቱ ናቸው። ለዚህ ትምህርት ምላሽ የሚሰጡና የኢየሱስን አምላክነት የሚያረጋግጡትን እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተመልከት /ኢሳ. 9:6፤ 10:21፤ ዮሐ. 1:1፤ 23፤ ኢሳ. 40:3፤ ዮሐ. 8:58፤ 12:37-41፤ ኢሳ. 6:1-10፤ ዕብ. 1:1-12፤ መዝ. 102:25-27፤ ራእይ 22:13/

ሐ/ የበታች፣ (Subordinationism)

ይህንን አመለካከት ያመነጨው አሪዓን የተባለው አስተማሪ ነው። የኖረውም ከ185-254 ዓ.ም. መካከል ባለው ዘመን ነበር። የትምህርቱ ጭብጥም አግዚአብሔር ወልድ ዘላለማዊና መለኮት ነው። ሆኖም ከአብ ያንሳል ወይንም የበታች ነው በማለት ያስተምር ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህን ዓይነቱን ትምህርት በመቃወም አብና ወልድ አንድ የማይበላለጡና እኩል መሆናቸውን በሚገባ ያረጋግጣል /ዮሐ. 10:30/።

መ/ ልጅነት፣ (Adoptionism)

ይህ የስሕተት ትምህርት የሚያስተምረው ኢየሱስ አስከ ጥምቀቱ ቀን ድረስ ተራ ሰው ሆኖ ይኖር እንደነበር ነው። ከዚያ በኋላ ግን አግዚአብሔር ኢየሱስን እንደ ልጁ በማድረግ መለኮታዊ ኃይልን እንደሰጠው ያስተምራል። ከተሰጠው ኃይል የተነሣም ታላላቅ ተአምራትን ማድረግ ችሏል ይላል።

ይህ ትምህርት የኢየሱስን ዘለዓለማዊነት አይቀበልም። አግዚአብሔር ኢየሱስን እንደ ልጁ አድርጎ ተቀብሎታል ቢልም መለኮታዊ ባሕርይ አንዳሰው ግን አያስብም። ትምህርቱ ኢየሱስ የከበረ ሰውና አግዚአብሔር «ልዩ ልጄ» ብሎ የጠራው ነው በማለት ይደመድማል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ኢየሱስ ዘላለማዊ የሆነ አምላክ መሆኑን በአጅጉ ያረጋግጣል /ኢሳ. 9:6፤ ዮሐ. 1:1፣ ራዕ. 22:13/።

ሠ/ አሃዳውያን (Monotheism)

እግዚአብሔር ሦስት አካላት ሳይሆን አንድ አካል ነው። እርሱም አብ ብቻ ነው በማለት የሚያስተምር ትምህርት ነው። አግዚአብሔር ወልድን በተመለከተ ሰው ብቻ ነው

ይላል። አብዛኛዎቹ የዚህ ትምህርት ተከታዮች ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ አንደሆነ አይቀበሉም። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለት ለአነርሱ ከእግዚአብሔር ጋር አኩል እንደማድረግ ሊሆን በሴላ በኩል ደግሞ አግዚአብሔር ይወልዳል ማለት ስለሚሆንባቸው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አይቀበሉትም። አስላሞችና የአይሁድ እምነት ተከታዮች የዚህ ትምህርት ደጋፊዎችና ተቀባዮች ናቸው።

ረ/ ክርስቲያን ሳይንስ (Christian Science)

የዚህ ትምህርት መሥራች ሜሪ ቤከር ኤዲ (Mary Baker Eddy) የምትባል ሴት ነች። ጊዜው አንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1886 ነበር። ይህ ትምህርት የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ መልበስ፣ ኃጢያት አለመፈጸም፣ መሰቀትነቱን፣ ፍጹም ሰው መሆኑን፣ ሥቃዩን፣ ሞቱን፣ ከሞት በአካል መነሣቱንና አርገቱን ሁሉ የሚክድ ነው። በአጠቃላይ የክርስቶስን ሞት ከደህንነት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም የሚል ትምህርት ነው። ለክርስቲያን ሳይንስ የእግዚአብሔር ማንነት ከመለኮታዊ አሳብ ያለፈ አይደለም። ይህ ትምህርት የክርስቶስን አምላክነትና የወንጌል ልብ/ማዕከል የሆነውን ሞቱን፣ መቀበሩንና በሦስተኛው ቀን ደግሞ ከሞት መነሣቱን /1ቆሮ. 15:3-4/ የሚክድ ስለሆነ ስሕተቱ የከፋ ነው።

ሰ/ ሞርሞን (Mormnns: The Church of Jesus Christ of Latter-Day Saints)

የእምነቱ መሥራች ጆሴፍ ስሚዝ ሊሆን፣ በቁጥር ጥቂት የሆኑ ጓደኞቹም አብረውት ነበሩ። ጊዜውም አንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1830 ነበር። እምነቱ በስድስት እባላት የተጀመረና ዛሬ ግን ከስድስት ሚሊዮን አባላት በላይ

ያስቆጠረ ነው። ሞርሞኖች መጽሐፍ ቅድሳዊ በሆነ ትምህርተ ሥላሴ አያምኑም። የእነርሱ የሥላሴ አስተምህሮ «ሦስት አምላኮች አሉ» የሚል ነው። ከአንድ በላይ አምላክ አሰ የሚሰውን አሳብ ሰማስረጃነት ከመጽሐፍ ቅዱስ አናገኝም።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርተ ሥላሴ የሚያረጋግጠው ሦስት አካላት በአንድ አምላክ ውስጥ ብቻ መገኘታቸውን ነው። አነርሱም ሦስት አምላኮች ሳይሆኑ በአንድ አምላክ ውስጥ የሚገኙ ሦስት አካላት ናቸው። አነርሱም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። በአያንዳንዱ አካልም የእግዚአብሔር መለኮት በሙላት ስላለ አግዚአብሔር አብ፣ አግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ አንጂ ሦስት አምላኮች አይደሉም።

ሞርሞኖች ይህም ሳይበቃቸው አግዚአብሔር እንደ ሰው ሥጋና ደም አንዲሁም አጥንት ጭምር ያለው ነው ይላሉ። ይህ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ከሚያስተምረው አሳብ ጋር በእጅጉ የሚቃረን ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በተመለከተ አንዲህ ይላልና። «እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በአውነት ሊሰግዱለት ይገባል» /ዮሐ. 4:24/። ስለሆነም አግዚአብሔር ሞርሞኖች አንደሚሉት ሥጋና ደም እንዲሁም አጥንት ያለው ሳይሆን መንፈስ የሆነ አምላክ ነው።

የሞርሞኖች አስተምህሮ «ሰዎች ወደ አምላክነት የመለወጥ ችሎታ አላቸው» በማለት ያስተምራል። የኢየሱስን ፍጹም አምላክነትም የማይቀበል ትምህርት ነው። አንዲያውም «ልክ እንደ እኛ የሆነ ሰው አንጂ የተለየ አይደለም» በማለት የሞርሞን ትምህርት ይሞግታል። ዘላለማዊ የሚሆነው

መንፈሱ ብቻ ነው። ይህም ልክ ሰው በመንፈሱ ብቻ ዘለለማዊ እንደሆነ የክርስቶስም እንደዚሁ ነው እያለ የሚያውጅ አስተምህሮ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ እምላክ እንደሆነ ያረጋግጣል /ኢሳ. 9:6፣ ራእይ 22:13/። ስለዚህ የሞርሞኖች ትምህርት የሥላሴን መሠረታዊ ትምህርት የሚቃረን ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔርና ስለሰው የሚያስተምረውን መልካም አሳብና ዓላማ ሁሉ የሚቃረን የስሕተት ትምህርት ነው።

6. ትምህርተ ሥላሴን የማጥናት አስፈላጊነት

ትምህርተ ሥላሴን እንድናጠናው ያስፈለገባቸው አምስት መሠረታዊ ምክንያቶች ቀጥሎው ያሉት ናቸው። እነርሱም

ሀ/ ከደህንነታችን ጋር የተያያዘ በመሆኑ

ለ/ የሦስቱን መለኮታዊ አካላት እንድነትና ልዩነት የሚያሳይ በመሆኑ

ሐ/ ለሦስቱም አካላት እምልክን ከማቅረብ ተገቢነት እንጻር

መ/ ሦስቱም አካላት ከጸሎታችን ጋር በመያያዛቸው ምክንያት

ሠ/ የእግዚአብሔርን ምሥጢር በመያዙ ምክንያት ነው። እነዚህን ነጥቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት ጥናታችን ከትምህርተ ሥላሴ ግንዛቤ እንዳይወጣ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ምዕራፍ ሰባት

መላእክት (Angels)

መግቢያ

መላዕክት የሚለው ቃል 'የመልእክ' ብዙ ቁጥር ነው። ትርጉሙም መልእክተኛ ወይንም ተላላኪ ማለት ነው። ቃሉ ወደ ሰዎች /ኢሳ. 44:26፣ ሚል. 2:7፣ ሉቃ. 7:24/ ወይንም ጠቅለል ባለ መልኩ መላእክት ብለን የምንጠራቸውን የመናፍስት የሥርዓት ለንለለት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል /ዘዳ. 33:2፣ /ሉቃ. 2:9፣ የሐዋ. 12:7/። በተጨማሪም የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች እግዚአብሔር እንዳንዴ ልዩ በሆነ ሁኔታ ራሱን በሚገልጥበት ጊዜ ይህን ልዩ የእግዚአብሔር መገለጥ ለማመልከት የጌታ መልእክ የሚለውን ሐረግ ተጠቅመዋል /ዘዳ. 3:2-6/።

ከላይ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ቅዱሳት መላእክት እንደሚናገሩ ከዓውዳቸው መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ርኩሳን ወይንም የወደቁ መላእክትም እንዳሉ ይነግረናል። «ታላቁ ዘንዶ፣ የጥንቱ እባብ ተጣለ፣ እርሱም ዲያብሎስ ወይንም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው፣ አለምን ሁሉ የሚያስተው ነው፣ እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፣ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ» /ራዕይ 12:9፣ በተጨማሪም ኢሳ. 14:12-15፣ ሕዝ. 28:11-19 ተመልከቱ/።

የሁለቱን መላእክት ልዩነት በኋላ እንመለከበታለን። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ከማንነታቸውና ከተግባራቸው አንጻር፣ «መላእክት ሁሉ መዳንን የሚወርሱትን ለማገልገል የሚላኩ አገልጋይ መናፍስት አይደሉምን?» /ዕብ. 1:14/ በማለት ቅዱሳን መላእክት «አገልጋይ መናፍስት» መሆናቸውን ያረጋግጣል። ይህ ማለት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው ለማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የመላእክትን መኖርና አገልግሎታቸውን በሰፊው ያስተምረናል። ጌታ ኢየሱስ ራሱ ደግሞ ስለ መላእክት ብዙ ተናግሯል። መላእክት ክዘላለም የነበሩ ሳይሆን የተፈጠሩ እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። /ነህ. 9:6፣ መዝ. 148:2, 5፣ ቆላ. 1:16፣ 1ጢሞ. 6:16/። የተፈጠሩበት ጊዜ በግልጽ ባይጻፍም እግዚአብሔር ሰማያትን በፈጠረ ጊዜ አብሮ እንደፈጠራቸው ይናገራል /ዘፍ. 1:1/። ወዲያው ስማያትን እንደፈጠረ አክታትሎ መላእክትን ፈጥሮአል ማለት ነው። ይህም ምድር ከመፈጠሯ በፊት እንደሆነ የብዙዎች እምነት ነው /ኢዮብ. 38:7/። መጽሐፍ ቅዱስ ቁጥራቸውን በግልጥ ባያስቀምጥም፣ እጅግ ብዙ እንደሆኑ ግን አሰፍሯል /ዳን. 7:10፣ ማቴ. 26:53፣ ዕብ. 12:22፣ 13:2/።

1. የአፈጣጠር ባሕርያቸው

ሀ/ መላእክት ክብርን የሚሰጡት ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር ነው

ለ/ መላእክት አካል የላቸውም

መላእክት በአፈጣጠራቸው ቁሳዊ አካል የሌላቸው መናፍስት ናቸው /መዝ. 104:4፣ ዕብ. 1:7, 14፣ ኤፌ. 6:12/። ነገር ግን ለሰዎች በሚገለጡበት ጊዜ በሥጋዊ አካል ይገለጻሉ /ዘፍ. 18:19፣ መሳ. 2:1፣ 6:11-24፣ ማቴ. 1:20፣ ሉቃ. 1:26፣ ዮሐ. 20:12፣ ዕብ. 13:2/።

ሐ/ መላእክት የሰው ዘር አይደሉም

መላእክት የሰው ዘር ሳይሆኑ የሰማይ ሠራዊት ናቸው /ዕብ. 12:22/። ክዚህ የተነሣ አያገቡም፣ አይጋቡምም /ሉቃ. 20:34-36/። ደግሞም የማይሞቱ ናቸው። በብሉይ ኪዳን አምስት ጊዜ ያህል የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ተጠርተዋል /ዘፍ. 6:2,4፣ ኢዮ. 1:6፣ 2:1፣ 38:7/። በመጽሐፍ ቅዱስ በተባዕታይ ፆታ (Masculine Gender)

ይገለጣሉ። ይሁን እንጂ የፆታ ሰንሰለት የላቸውም። ስለሆነም ራሳቸውን ችለው በእግዚአብሔር ለእንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተፈጠሩ ናቸው። የሚራቡና የሚባዙም አይደሉም።

መላእክት ኃጢያትን የሚያደርጉት በራሳቸው ተነሳሽነትና በግላቸው ነው። የጋራ የሆነ ፀባይም የላቸውም። ማለትም እንደ ሰው ልጆች በትውልድ የሚተላለፍ የጋራ የሆነ ነገር የላቸውም። ይህም የሆነበት ምክንያት ስለማይጋቡና ስለማይራቡ ነው። እንዲያውም የሚገለጡበት ፆታ አንድ ዓይነት ወንድ ነው። አንድ አይነት የሆነና በትውልድ የሚተላለፍ ባሕርይ ስለሌላቸው በኃጢያት በወደቁ ጊዜ ለዘላለም ፍርድ የተተውት በዚህ ምክንያት መሆኑ ይታመናል። ደህንነትን ላያገኙ የቀሩበትም ምክንያት ይኸው ነው።

ሰው ግን የጋራ የሆነ ባሕርይ/ፀባይ አለው። ይህም ከትውልድ ለንሰለት የተገኘ ወይንም የተላለፈ ነው። ያውም ከአዳም ነው። ሰው ከአዳም የወረሰው የአዳምን ለብአዊ ተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን ኃጢአትንም ጭምር ነው። ስለሆነም ክርስቶስ ሞትን ከሚያስከትለው ኃጢአት ሰውን ለማዳን መጣ /ማር. 10:45/። ለብሶት የመጣው ግን የመላእክትን ተፈጥሮና ባሕርይ ሳይሆን የሰምችን ነው /ዕብ. 2:16/። ጌታ ክርስቶስ ይህን በማድረጉ ከዘላለም ፍርድ አመለጥን /ሮሜ. 8:1-2/።

መ/ መላእክት በእውቀት ከሰዎች የበለጡ ናቸው

መላእክት በእውቀታቸው ከሰዎች ይብለጡ እንጂ እንደ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የሚያውቁ አይደሉም /ማቴ. 24:36/። ስለሆነም እውቀታቸው ገደብና መጠን ያለው ነው።

ሠ/ መላእክት በጉልበት/ኃይልም ከሰዎች የበረቱ ናቸው

መላእክት ከሰው የላቀ ጥንካሬና ጉልበት ቢኖራቸውም ሁሉን ማድረግ ግን የሚችሉ አይደሉም። ስለሆነም ችሎታቸው ገደብ አለው። ተግባራቸውም የጥንካሬያቸውን ውስንነት ያሳየናል /መዝ. 103:20፣ 2ኛ ጴጥ. 2:11፣ 2ኛ ተሰ. 1:7፣ የሐዋ. 5:19፣ 12:7 23፣ ማቴ. 28:2/።

2. የመላዕክት ውድቀት

እግዚአብሔር አምላክ የወደቁ መላእክትን ጨምሮ ፍጥረትን ሁሉ መልካም አድርጎ እንደፈጠረ በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ተጽፎአል። ከዚህ በኋላ ግን በራሳቸው ተነሳሽነት ከፋትን ሰላደረጉ ሊወድቁ ቻሉ /2ኛ ጴጥ. 2:4/። የከፋትና የጥፋት መላእክትም ተብለው ተጠሩ /መዝ. 78:49፣ ማቴ. 25:41፣ ይሁዳ 6/። ሰይጣን መጀመሪያ ከወደቀ በኋላ /ኢሳ. 14:12፣ ሕዝ. 28:15-17/ ሰሌሎች መላእክትም ሁሉ የመውደቃቸው ምክንያት እንደነበር የሚያጠራጥር አይደለም /ራእይ 12:9/።

ሀ/ መላእክት የወደቁበት ጊዜ

በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ መላእክት የወደቁበት ጊዜ መቼ እንደነበር ተጽፎ አናገኝም። ነገር ግን የመላእክት ውድቀት ከሰው ልጅ ውድቀት በፊት እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቁመናል /ዘፍ. 3/። ከዚህ ተነሥተን ግን የውድቀታቸውን ጊዜ ስማስቀመጥ ብንሞክር እንሳሳታለን። ስለዚህ ጉዳይ የመጻሕፍት ሁሉ አለቃ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ዝም ብሏልና እኛም ዝም ብንል ይበጀናል። ሆኖም በዚህ ነጥብ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች ስላሉ እነርሱን ቀጥለን መመልከት እንችላለን።

1/ መላእክት የወደቁት ከፍጥረት አፈጣጠር ጀምሮ ሰው እስከ ወደቀበት ባለው የጊዜ ገደብ መካከል ነው የሚል።

2/ በዘፍ. 1:2 ላይ ትልቅ ጥፋት እንደነበር ይጠቁማልና የመላእክትም ውድቀት ያን ጊዜ እንደሆነ የሚገልጽ ነው የሚል።

3/ ሌሎች ደግሞ በ1 እና በ2 ተራ ቁጥሮች የተሰጡትን አመለካከቶች በመገምገም መላእክት የወደቁት እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ከሠራ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ነው በማለት ይገምታሉ።

ለ/ መላእክት የወደቁበት ምክንያት

ስመላእክት ውድቀት መነሻ የሆነው ኃጢያትን ለማድረግ ሆን ብለው መፍቀዳቸውና መወሰናቸው ነው /ኢሳ. 14:13-14፣ ሕዝ. 28:11-19፣ 1ኛ ጢሞ. 3:6/። የመጀመሪያውና ቀስቃሹ ግን ዲያብሎስ ነው። ስለሆነም እርሱ ስሜረው ዓመጽ ምክንያት ውድቀቱ ሰሌሎችም መላእክት ተረፈ /ራእይ. 12:9/።

ሐ/ የመላእክት ውድቀት ውጤት

1/ የቀድሞውን ቅድስናቸውን በመጣላቸው ተፈጥሮአቸውና ፀባያቸው የተበላሸ ሆነ /ማቴ. 10:1፣ ኤፌ. 6:11-12፣ ራእይ 12:9/።

2/ ወደ ምድር ተጣሉ /ራእይ 12:9/።

3/ የቅዱሳን መላእክትን አገልግሎት ወደ መቃወም መጡ /ራእይ 12:79፣ ዳን. 10:12-13፣ 20-21፣ ይሁዳ 9/።

4/ በፍጥረታት ላይ ተጽእኖ አደረጉ /ዘፍ. 3:17-19፣ ሮሜ. 8:19-22/

5/ ከእነርሱ መካከል እግዚአብሔር እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በጎሄነም ውስጥ ያሰራቸው አሉ /2ኛ ጴጥ. 2:4/።

6/ ወደ ዘላለም እሳት የመጣል ፍርድ /ማቴ. 25:41፣ 2ኛ ጴጥ. 2:4፣ ይሁዳ 6/።

3/ የመላእክት ድልድል (The Classification of the Angels)

መላእክት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይደለደላሉ። አነርሱም ቅዱሳንና /Holy Angels/ የክፋት መላእክት /fallen or evil angels/ በመባል ይታወቃሉ።

ሀ/ ቅዱሳን መላእክት

እነዚህ ቅዱሳን መላእክት እንደገና በእራት ክፍሎች ይከፈላሉ። እነርሱም፣

1/ መላእክት (The Angels)

«መልአክ» የሚለው ቃል ስዕብራይስጥና ስግሪክ ቋንቋ ትርጉሙ እንድ ዓይነት ነው። ይኸውም «መልአክተኛ» ማለት ነው። የእንግሊዝኛው ቃል "Messenger" ማለት ነው። እነዚህ ቋንቋዎች ሰያይተው የማያስቀምጡ ስለሆነ የሰው መልእክ ወይንም ሰማያዊ መልአክ መሆኑን የምናውቀው በቃሉ አገባብ ብቻ ነው። በአብዛኛው ግን የቃሉ ዓውድ የሰማይ መልእክን ወይንም መላእክትን የሚጠቁም ነው። ይሁን እንጂ አልፎ አልፎም ቢሆን ወደ ሰውም የሚያመለክትበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ በሉቃስ 7:24 ላይ ስዮሐንስ መልእክተኞች የተሰጠው ቃል "Angels or Messengers" የሚለው ነው። የቃሉ አገባብ ወደ ሰው ማመልከቱን ከጥቅሱ ዓውድ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

የለባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ተብሎ በራእይ ምዕራፍ 2 እና 3 ላይ የተጠቀሰው ቃልም ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። በእነዚህ ምዕራፎች ላይ የተጠቀሱት መላእክት የሰማይ መላእክት እንደሆኑ የሚያረጋግጥ አሳብ የለም። ይልቁንም

የቤተክርስቲያን መሪዎች ናቸው የሚለው አሳብ ብዙዎች የሚስማሙበት ነው። ስዚህ እንደመረጃ የሚቀርበው ነጥብ የቤተክርስቲያን መሪዎች ዮሐንስን ስመጎብኘት ወደ ፍጥሞ ደሴት በመጡ ጊዜ መልአክቱን በአነርሱ እጅ ወደ አብያተ ክርስቲያናት በመላኩ ምክንያት መልእክ/መላእክት (Angels or Messengers) የሚል መጠሪያ ስም ተሰጣቸው የሚል ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ የሚጠቀሱ የሰማይ መላእክት ናቸው። በቁጥር ብዙ ሲሆኑ አገልግሎታቸውንም በእግዚአብሔር ፊት በመቆም ያከናውናሉ /ዳን. 7:10፣ ዕብ. 12:22/። ቅዱሳንንም ክሥጋዊና ክመንፈሳዊ ጉዳት ስመጠበቅ በአግዚአብሔር የተሾሙም ናቸው /መዝ. 34:7፣ ማቴ. 26:53/። እነዚህ መላእክት ክንፍ እንዳላቸውም መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል /ዳን. 9:21፣ ራእይ 4:6-11፣ 14:6/።

2/ ኪሩቤል /በዕብራይስጥ ኪሩብ (ነጠላ ቁጠር) ኪሩብም (የብዙ ቁጥር)

ኪሩቤል /ኪሩብም/ የብዙ መላእክት መጠሪያ ስም ነው። ብዙ ጊዜም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ሰማያውያን ፍጥረታት ናቸው። እነዚህም ኪሩቤል በኃጢአት የወደቀው የሰው ልጅ ዳግም ወደ ኤድን ገነት ዝር እንዳይል መንገዱን ይጠብቁ እንደነበር ክመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን /ዘፍ. 3:24/። በሌላ በኩልም ደግሞ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሁለት ክወርቅ የተሠሩ ኪሩቤል በክንፎቻቸው የስርየት መክደኛውን ይሸፍኑት እንደነበርና እግዚአብሔር በዚያ ሆኖ ለእስራኤል ልጆች በሙሴ በኩል ይናገራቸው እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል /ዘጸ. 25:18-22/። ይህም ብቻ ሳይሆን በድንኳን

መጋረጃዎችም ላይ የኬሩቤል ምስል ይታይ እንደነበር ተጽፏል /ዘጸ. 26:1/። በእነዚህም ኪሩቤል መካከል በመሆን እግዚአብሔር ለሙሴ መመሪያን ያስተላልፍ ነበር /ዘኁ. 7:89/።

ንጉሥ ሰለሞንም ቤተ መቅደሱን በሠራ ጊዜ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ከወይራ እንጨት የተሠሩትን ሁለት የኪሩቤል ምስሎች እቁሞ እንደነበር ተጽፎ ይገኛል /1ነገ. 6:23/። ለነቢዩ ሕዝቅኤልም ታይተውት የነበሩ ኪሩቤል የሰው፣ የእንበሳ፣ የላምና/በሬ/፣ የንስር ፊት እንደነበራቸው እናነባለን /ሕዝ. 1:5-28/። ሐዋርያው ዮሐንስም በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ሲቆሙ የተመለከታቸው አራቱ እንስሶች የተባሉት እነዚህን በሕዝቅኤል ላይ የተጠቀሱትን የሚመስሉ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስነብበናል /ራእይ 4:6-11/።

ኪሩቤል ደግሞ የእግዚአብሔርን ቅድስናና ግርማ የሚያውጁ እንደሆኑም በሕዝቅኤልና በዮሐንስ ራእይ ከተጠቀሱት ክፍሎች መረዳት ይቻላል። ኪሩቤል ለእግዚአብሔር ክብር በዙፋኑ ዙሪያ የሚቆሙም ናቸው። የእግዚአብሔርም እምባሳደር ናቸው። ኃይልን በመጠቀም ፍርዱንም ይፈጽማሉ። ስለ ኪሩቤል 2ኛ ነገ. 19:15፣ ሕዝ. 10:1-20፣ 28:14-16፣ በተጨማሪ ተመልከት።

3. ሱራፌል

ሱራፌል/ሱራፍም ቃሉ የዕብራይስጥ ሲሆን ቁጥሩ ደግሞ የብዙ ነው/ ኢሳይያስ 6:2፣ 6 ላይ ብቻ በስም ተጠቅሰዋል። ሱራፌልም በራእይ ለኢሳይያስ የታዩና በእግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ የሚያገለግሉ ሰማያዊ ፍጥረቶች ናቸው /ኢሳ. 6:1-7/።

ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን እምልክ ይመራሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣ ያጣራሉም። ይህን ስንመለከት አገልግሎታቸው ከአምልኮ ጋር የተያያዘ መሆኑን መረዳት እንችላለን። በታላቅ ትሕትና ይኹንን አገልግሎት ይፈጽማሉ። ሱራፌል ከኪሩቤል ልዩነት አላቸው። ያውም እግዚአብሔር በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ ሲሆን /መዝ. 80:1፣ 99:1/፣ ሱራፌል ግን ከእርሱ በላይ የሚቆሙ ናቸው/ኢሳ. 6:2/።

4. የመላእክት አለቆች (Archangels)

የዕብራይስጥ ትውፊት /Hebrew Tradition/ 12 የሚሆኑ የመላእክት አለቆች እንዳሉ ይጠቁማል። ይሁን እንጂ የመላእክት አለቃ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ የምናገኘው ሁለቱ ብቻ ነው /1ኛ ተሰ. 4:16፣ ይሁዳ 9/። ከዚህ እንጻር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ በስም የሚጠቅሰው ሚካኤልን ብቻ ነው /ይሁዳ 9/። /ሚካኤል ማለትም እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን ነው ማለት ነው/ ስለዚህ መልእኩ ሚካኤል የመላእክት አለቃ ነው። ከሥራም ተከታዮች እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ ይዘግባል /ራእይ 12:7/። ስለእስራኤል ልጆችም እንደ አለቃ ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል /ዳን. 10:13፣ 21፣ 12:1/።

መልእኩ ገብርኤል /ገብርኤል ማለት የእግዚአብሔር ብርታት ማለት ነው/ ከሚካኤል ቀጥሎ ሁለተኛ አለቃ እንደሆነ ይታመናል። የእነዚህ መላእክት ሥራ እስራኤላውያንን በመጠበቅ ላይ ያተኮረ ቢሆንም /ዳን. 10:13፣ 21፣ 12:1/ ተጨማሪ ተግባራትና ኃላፊነትም አላቸው። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የጌታን መወለድ ማወጅ /ሉቃ. 1:26-28/

ሰ/ ስይጣንና ተከታዮቹ የሆኑትን የክፋት መላእክት መምታት /ራእይ 12:7-12/

ሐ/ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት ማወጅ /1ኛ ተስ. 4:16/

- መልአኩ ሚካኤል ሰመልካምና ሰበጎ ነገር ለእስራኤል እሰቃ እንደሆነ ሁሉ የክፋት መላእክት ደግሞ ክፋትንና ጥፋትን በማሠራጨት በእያንዳንዱ አገር ላይ የተመደቡ ናቸው። /ዳን. 10:20/

4. የቅዱሳን መላእክት ሥራ (The Work of the Holy Angels)

ሀ/ የጌታን ሕይወትና አገልግሎት በተመለከተ

1. ማርያም የአዳኙ ጌታ ፡ እናት እንደምትሆን ተናግረዋል /ሉቃ. 1:26-38/።
2. የማርያም ጽንስ ከመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ የማርያም እጮኛ ሰሆነው ዮሴፍ ገልጸዋል /ማቴ. 1:20/።
3. ጌታ በቤተልሔም መወለዱን ለእረኞች አብስረዋል /ሉቃ. 2:8-15/።
4. ጌታ በምድረበዳ በስይጣን በተፈተነ ጊዜ አገልግለውታል /ማቴ. 4:11/።
5. በእትክልቱ ሥፍራ ጌታን አበረታትተውታል /ሉቃ. 22:43/።
6. በፍልሚያ ጊዜ አስፈላጊ ከሆነ ጌታን ለመርዳት ዝግጁ ነበሩ /ማቴ. 26:53/።
7. የመቃብር ድንጋይ አንከባልለዋል /ማቴ. 28:2-7/።
8. በአርገቱ ጊዜ ጌታን እጅበዋል /የሐዋ. 1:11/።

9. በምጽአቱ ጊዜም ደግሞ ጌታን ያጅቡታል /ማቴ. 16:27፣ 25:31/።

ለ/ አጠቃላይ የሆነ የቅዱሳን መላእክት ሥራ

1. በእግዚአብሔር ፊት በመቆም ማምለክ /ማቴ. 18:10፣ ራዕ. 5:11፣ መዝ. 148:2፣ ዕብ. 1:6/።
2. የእግዚአብሔርን ሕዝብ መጠበቅ /ዘፍ. 19:11፣ 1ኛ ነገ. 19:5፣ መዝ. 91:11፣ የሐዋ. 12:11፣ ዳን. 10:13፣ 21፣ 3:28፣ 6:22፣ የሐዋ. 5:19፣ ዕብ. 1:14፣ ዳን. 12:1።
3. የእግዚአብሔርን ባሪያዎች መምራትና ማበረታታት ማቴ. 28:5-7፣ የሐዋ. 8:26፣ 27:23-24/።
4. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሰዎች መተርጎም /ኢዮ. 33:23፣ ዳን. 10:5፣11. ዘካ. 1:9፣ 13-14፣ 19፣ ዘካ. 2:3፣ 4:1, 4, 5፣ 5:5, 10፣ 6: 4-5/።
5. የእግዚአብሔርን ፍርድ በማስፈጸምና በአገር ላይ መፈጸም /የሐዋ. 12:23፣ ዘፍ. 19:12-13፣ 2ኛ ሳሙ. 24:16፣ ሕዝ. 9:1, 5, 7፣ ራእይ 15/።
6. በጌታ የሞቱትን ወደ ጌታ አቅፍ መውሰድ /ሉቃ. 16:22/።

ሐ/ የቅዱሳን መላእክት የወደፊት አገልግሎታቸው

1/ ጌታን ሲመለስ ማጀብ /1ኛ ተስ. 4:16/።

2/ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ የጌታን ምርጦች መስብሰብ (ይህ ለእስራኤል ሕዝብ የተነገረ ነው ተብሎ ይታመናል) ማቴ. 24:31።

3/ ጌታ ሲመጣ ስንዴን ከእንክርዳዱ መሰየት /ማቴ. 13:39፣ 49፣ 50/::

4/ በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም በር ሳይ መቆም /ራእይ 21:22/

ለ/ የክፋት መላእክት (The Evil Angels)

የክፋት መላእክት በአራት ዋና ዋና ምድቦች ይከፈላሉ:: እነርሱም

1/ ታስረው ያሉ የክፋት መናፍስት (The angels that are Kept in Prison)

እነዚህ የክፋት መናፍስት በጴጥሮስና በይሁዳ መልእክቶች ተጠቅሰዋል /2ኛ ጴጥ. 2:4፣ ይሁዳ 6/:: ስሰ እነዚህ የክፋት መላእክት በሁሰቱም አገልጋዮች እእምሮ ውስጥ የነበረው አንድ አይነት አስተሳሰብ ነው:: ይሁን እንጂ በሰዚህ ጉዳይ በሌሎች ሰዎች የተሰያዩ አመለካከቶች ይሰነዘራሉ::

2.1 እነዚህ የክፋት መላእክት የፈጸሙት ኃጢአት በዘፍ. 6:2 ሳይ የተጠቀሰው ነው በማለት ይደመድማሉ:: ሲያብራሩም የእግዚአብሔር ልጆች የሚሰው ሐረግ የሚያመሰክተው መላእክትን ነው /ኢዮ. 1:6፣ 2:1/:: «ስለሆነም ከሰው ሌቶች ልጆች ጋር ተጋብተዋልና እግዚአብሔር ደግሞ ይህን በመሰለ ፍርድና ቅጣት ሥር እንዲወድቁ ወሰነ» የሚል አመለካከት ነው:: ይሁን እንጂ አመላእክት አፈጣጠር ባሕርይ አኳያ ሲታይ፣ አመለካከቱ የማያስኬድ ነው:: ምክንያቱም መላእክት መናፍስት ስለሆኑ ቢጋቡኞ የመራባት ባሕርይ

እንደሌላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ወበጥ የተጻፈ በመሆኑ ነው/ሉቃ. 20:34-36/:: ሌላው ደግሞ የመላእክት በጋጢአት ምክንያት መውደቅና መጣል ከዘፍ. 6 ታሪክ በፊት መሆኑ /ዘፍ. 3/ አመለካከቱን ሰመቀበል አበቸጋሪ ያደርገዋል::

2.2 የሁለተኛው አመለካከት አቅጣጫ እጅግ ከፉ የሆኑ የክፋት መላእክት በሰሆኑ ከመጨረሻው ፍርድ በፊት ገሃነም በሆነው በጨለማ ጉድጓድ ውበጥ መቆየት በለነበረባቸው ነው የሚል ነው:: ይሁን እንጂ ከወደቁት መላእክት መካከል አንዳንዶቹ ሲታሠሩ ሌሎቹ ደግሞ አጋንንት ሆነው ሳሉ ለይጣንን ሰማገልገል ሰምን በነጻነት እንደተለቀቁ በመጽሐፍ ቅዱስ ወበጥ ምክንያቱ ተጽፎ አይገኝም:: ስለሆነም ሁለተኛውንም አመለካከት ለመቀበል በቂ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ስለሌለ አበቸጋሪ ነው:: ከዚህ የተነሣም ማንም በትክክል ይኼ ነው ሲል አይችልም::

2/ በነጻነት የተለቀቁ የክፋት መናፍስት

እነዚህ የክፋት መላእክት በመጽሐፍ ቅዱስ ወበጥ የተገለጹት መሪያቸው ከሆነው ከለይጣን ጋር በተያያዘ መልኩ ነው /ማቴ. 25:41፣ ራዕ. 12:7-9፣ መዝ. 78:49፣ ሮሜ. 8:38፣ 1 ቆሮ. 6:3፣ ራዕ. 9:14፣ ኤፌ. 1:21፣ 6:12፣ ቆሳ. 2:15/:: ትልቁ ሥራቸው መሪያቸው የሆነው ለይጣን ከቅዱሳን መላእክት ጋርና ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በሚዋጋበት ጊዜ እርሱን መርዳት ነው::

3/ አጋንንት/ርኩሳን መናፍስት (The demons or evil or unclean spirites)

አጋንንት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁለት ቦታ ብቻ ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን /ዘዳ. 32:17፣ መዝ. 106:37/:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ግን አጋንንት (The demons) ብቻ ሳይሆኑ ርኩሳን መናፍስት (evil spirits) የሚባሉም ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለቱም በብዛት ተጠቅሰዋል:: በሁለቱ መካከል ልዩነታቸውን የሚያሳይ የጎላ መስመር ስለሌለ ሊኖራቸው ስለሚችለው ልዩነት መጨነቅ የለብንም:: በሰነርሉ ልናውቀው የሚገባ አንኳር ነጥብ ቢኖር ጥፋትንና ጉዳትን ለማድረስ ሰይጣንን የሚከተሉ የክፉት መናፍስት መሆናቸውን ነው /ሉቃ. 10:17-20/:: በርግጥ ደረጃቸውና አይነታቸው ብዙ ሊሆን ይችላል /ኤፌ. 6:12/::

አጋንንት ወይንም ርኩሳን መናፍስት ወይንም ንጹህ ያልሆኑ መናፍስት ኢየሱስ ክርስቶስን ሰይተው ያውቁታል /ማቴ. 8:29፣ ማር. 5:6-8/:: እግዚአብሔርም በዙፋኑ ላይ በኃያልነቱ እንዳሰ በማበተዋልም በፍርሃት የሚንቀጠቀጡ ናቸው /ያዕ. 2:19/::

መናፍስት በሰው ብሎም በእንስሳት ውስጥ ሲገቡ ይችላሉ /ማር. 5:9-20/:: አጋንንት በጣዖት ዘንድም ይገኛሉ /1ኛ ቆሮ. 10:20-22፣ ራእይ 9:20/:: በቤተክርስቲያንም ውስጥ በመግባት ሰዎችን የማታለል ተግባር ያራምዳሉ /1ኛ ጢሞ. 4:1/:: የቀትር ስዓት ደግሞ እነርሱ በእጅጉ የሚሰሰጥኑበት ጊዜ ነው /መዝ. 91:6/::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር አገልግሎቱ ዘመን ከብዙ ሰዎች አጋንንትን አስወጥቷል:: ከዚህ የተነሣም ፈሪሳውያን ኢየሱስ በአጋንንት ሥልጣን አጋንንትን ያወጣል በማለት አገልግሎቱን ለማዛባት ሞክረው ነበር /ማቴ. 12:22-30/:: እርሱ ግን ለተከታዮቹም ሥልጣንን በመስጠት አጋንንትን በስሙ አንዲያወጡ አደረገ /ሉቃ. 9:1፣ 10:17/:: ለአማኞች ሁሉ እንዲህ ዓይነቱ ሥልጣን ተሰጥቷል /ማር. 16:17/:: ከአስራት የተፈታው ሰው ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልቶ በጌታ ካልበረታ በስተቀር አጋንንቱ ሊመለስበት ይችላል /ማቴ. 12:43-45/::

«አጋንንት ወይንም ርኩሳን መናፍስት ወይንም ንጹሕ ያልሆኑ መናፍስት እነማን ናቸው?» ብለን በምንጠይቅበት ጊዜ ትንሽ ድንግርግር የሚል ሁኔታ ሊገጥመን ይችላል:: በሰሁሉም በዚህ ነጥብ ላይ ሦስት የተለያዩ አመለካከቶች እንደሚከተለው ተሰንዝረዋል::

ሀ/ የመጀመሪያው አመለካከት አጋንንት ወይንም ርኩሳን መናፍስት ወይንም ንጹሕ ያልሆኑ መናፍስት በሞት ያለፉ የኃጢያተኞች ሰዎች መንፈስ/ነፍስ ናቸው የሚል ነው::

- ይህን ሐሳብ እንዳንቀበል መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአተኞች መንፈስ/ነፍስ በምድር ላይ በነጻነት እንዳትዘዋወር በሲኦል ውስጥ እንደምትጠበቅ ይናገራል /መዝ. 9:17፣ ሕዝ. 32:17-24፣ ሉቃ. 16:23፣ ራእይ 20:13/:: በተጨማሪም የሲኦል ቁልፍ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ስለሆነ፣ ወጥተው እንደፈለጉ እንዲሆኑ አይፈቅድላቸውም /ራእይ 1:18/:: እዚህ ላይ

የሳሙኤልን መንፈስ ስላስነሣችው የዓይንዶር ነዋሪ ሴት ጉዳይ ሊነሣ ይችል ይሆናል።

- የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ሴትዮዋ ከስይጣን መንፈስ ጋር ግንኙነት በማድረግና በዚሁ መንፈስ ሳሙኤልን መሰል ሰው በመላብ ከላአል ጋር እንዳገናኘችው ያምናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ያወግዛል እንጂ አይቀበልምና ነው። «በመካከልህ ወንድ ወይንም ሴት ልጁን በእሳት የሚሠዋ ሟርተኛ ወይንም መተተኛ፣ ሞራ ገላጭ፣ ጠንቋይ፣ ወይንም በድግምት የሚጠነቁል፣ መናፍስት ጠሪ ወይንም ሙት አነጋጋሪ በመካከልህ ከቶ አይገኝ። እነዚህን የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነውና» /ዘዳ. 18:10-12/ በማለት እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት እንደሚጠላ መጽሐፍ ቅዱስ አስምሮበታል። ለይጣን ራሱን እንደፈጠገ መሰዋወጥ የሚችል ነውና ይህ የሚያስደንቅ አይደለም /2 ቆሮ. 11:14/።

ለ/ ሁለተኞቹ ክፍሎች ደግሞ አጋንንት ወይንም ርኩሳን መናፍስት የወደቁት መላእክት ናቸው ይላሉ። በአሁኑ ሰዓትም የክፋትን ተግባር ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ ናቸው እንጂ በገሃነም /በሲኦል ውስጥ የተዘጋባቸው አይደሉም በማለት ለዚህ አመለካከታቸው ቀጥለው ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ መረጀዎች ይጠቅሳሉ /ዳን. 10:13፣ 20፣ ራዕ. 12:7-9/።

- በ «ሀ» ሥር ከተጠቀሰው አሳብ ይልቅ ይኼኛው ከፍተኛ ተቀባይነት እንዳለው

ይታመናል። ሆኖም ግን ይህን አመለካከት በተመለከተ ሌሎች ሰዎች የሚያነሡት ተጨማሪ ነገር አለ። ይኼውም እነዚህ የወደቁት መላእክት የቅርብ ወዳጅነትን በመፍጠር በለው ውስጥ ገብተው ስመኖር ያደረጉት ነገር የለም ይላሉ። ሁለተኛው ነገር ደግሞ የወደቁት መላእክት በስው ውስጥ ገብተው ይኖራሉ ማለት የማይጣጣምና የማይመስል ነገር ነው ይሉና የወደቁ መላእክትና አጋንንት ወይንም ርኩሳን መናፍስት ተመሳሳይ ናቸው ካሳልን በስተቀር በማለት አሳባቸውን ያስቀምጣሉ።

- ሁለቱንም አሳብ የሚያስተናግዱ ሰዎች አንድ ነገር በሚገባ ያልተረዱ ይመስላሉ። ይኼውም የወደቁት ወይንም የክፋት መላእክት እነማን መሆናቸውን በሚገባ ያለማጤን ችግር ነው። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ሁሉ የታሠሩ፣ በነጻነት የሚዘዋወሩ አጋንንት/ርኩሳን መናፍስትና ስይጣንንም ጨምሮ ሁሉም የወደቁ መላእክት ናቸው። እነዚህ የወደቁ መላእክት ዳግም ባልተወለደና በመንፈስ ቅዱስ ባልተሞላ ስው ውስጥ ሲገቡ የሚችሉ ናቸው /ማቴ. 12:43-45/። ምክንያቱም አጋንንት ከወደቁ መላእክት መክክል ናቸውና ነው። በርግጥ በደረጃቸውና በዓይነታቸው ሊለያዩ ይችላሉ። ስለሆነም አጋንንትን ወይንም ርኩሳን መናፍስትን ከወደቁት መላእክት የተለዩ ናቸው ብሎ ማሰብ መደናገርን ያስከትላል።

ሐ/ በሦስተኛ ደረጃ የሚጠቀሱት ወገኖች ደግሞ ርኩሳን መናፍስት የተባሉት ፍጥረታት አካል የሌላቸውና ከአዳም ዘር መፈጠር በፊት የነበሩ መናፍስት ናቸው የሚሉ ናቸው። ይህም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም ተብሎ ውድቅ ተደርጓል። ይሁንና በዘፍ. 1:1-2 ባለው ክፍል የተዘገበው ታሪክ የለይጣንን፣ የመላእክቱና የኢጋንንትን ውድቀት የማያበስር ነው ብሎ የሚያምን ክፍል አለ።

ክላይ የተጠቀሰው ቡድን ሰይጣንና መላእክቱ በወደቁ ጊዜ ከእነርሱ ጋር የወደቁና በምድር ላይ ይኖሩ የነበሩ ዘር የሆኑ መኖራቸውን ይቀበላል። ሰይጣንም ደግሞ በእነርሱ ላይ ገዥ እንደነበረ አበክሮ ያምናል። በመቀጠልም እነዚህ በወደቁ ጊዜ እግዚአብሔር እካል አልባ በማድረግ ቀጣቸው ይላል።

ይህም ቅጣት ለይጣንና ተክታዩቹ ለመጨረሻ ፍርድ ወደ ገሃነመ እሳት አስኪጣሉ ድረስ የሚጸና ነው ብሎ ይደመድማል። የዚህ ቡድን ማስረጃም /2 ጴጥ. 3:5-6/ ያለው ነው። ይህ ቡድን እነዚህ አጋንንት ናቸው በማለት ያስምርበታል። እነዚህ ያለ አካል የሆኑ አጋንንት ደግሞ ዳግም በአካል ወይንም በሰውነት ቅርጽ /Re-embodiment/ ለመገኘት ሊሉ በሰው ውስጥ ይገባሉ ይላል።

ምላሽ

እጋንንት ወይንም ርኩሳን መናፍስት ማለት ሰይጣን ማለት አይደሉም። ነገር ግን አጋንንት

ወይንም ርኩሳን መናፍስት ልዩነት የላቸውም /ማቴ. 8:16፣ 10:1፣ 10:8፣ ሉቃ. 17:20፣ ኤፌ. 6:12/።

4/ ሰይጣን

ለይጣን የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ዲያብሎስ ደግሞ በግሪኩ ነው። ስሙ በቋንቋዎች ልዩነት ምክንያት ሁለት ይሁን እንጂ ትርጉሙ ግን ተመሳሳይ ነው። ያውም አሰናካይ፣ ተቃዋሚ ወይንም ክላሽ ማለት ነው። ለይጣን የወደቁት መላእክት አለቃና /ራእይ 12:9/ የመልካም ነገር ሁሉ ተቃራኒ ነው /ማቴ. 25:41/። ሰይጣን ሲፈጠር ቅዱስ ሆኖ የተፈጠረ፣ አግዚአብሔር ክፈጠራቸው ፍጥረታትም ሁሉ ከፍተኛ ውን ስፍራ የተቆናጠጠና የመላእክት ሁሉ አለቃ ኪሩብ የነበረ ነው። በኋላ ግን በትዕቢቱ ምክንያት ወደቀ /ኢሳ. 14:12-20፣ ሕዝ. 28:12-19፣ 1ጢሞ. 3:6/። እግዚአብሔርንም በመዳፈር የመልካም ነገር ሁሉ ተቃዋሚ ሆነ። የራሱን መንግሥት ሊያስፋፋ በብርቱ አንቅስቃሴ ላይ እያለም ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወቱና በመሰቀሉ ድል ነሣው። በዓለም ፍጻሜ ላይም ሰዘላለም ይፈረድበታል /ማቴ. 4: 1-11፣ ዮሐ. 12:31፣ ቆላ. 2:15፣ ራእይ 20:10፣ 1ኛ ዮሐ. 3:8/።

ለይጣን ሌሎችም በርካታ ስሞች አሉት። እነርሱም ዲያብሎስ /ማቴ. 4:1፣ 1 ዮሐ. 3:8/፣ ብዔልዜቡል፣ አብዶንና አጵልዮን /ራእይ 9:11/፣ የወንድሞች ክላሽ /ራእይ. 12:10/፣ ባለጋራ /1ኛ ጴጥ. 5:8/፣ የዓለም ሁሉ አለች ታላቁ ዘንዶ፣ የቀደመው እባብ /ራዕ. 12:9/፣ ክፉው /ማቴ. 13:19/፣ ነፍስ ገዳይ፣ የሐሰት አባት /ዮሐ 8:44/፣ የዚህ ዓለም ገዥ /ዮሐ. 12:31/፣ የዚህ ዓለም አምላክ /2ኛ ቆሮ. 4:4/፣ በአየር ላይ ሥልጣን

ያለው አለቃ /ኤፌ. 2:2/፣ ፈታኝ /1ኛ ተሰ. 3:5/፣ የሚያገሳ አንበሳ፣ /1ኛ ጴጥ. 5:8/ በመባል ተጠርቷል።

5. የወደቁ መላእክት ሥራ /The Work of the Fallen Angels/

ሀ. የክፋት መላእክት ሥራ

1. ክፋትን በሚሠሩና የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራ በሚጸረሩ ሰዎች ላይ መቅሰፍትን፣ መዓትንና መከራን እንዲፈጽሙ እግዚአብሔር ይጠቀምባቸዋል /መዝ. 78:49/።
2. አማኞችን ክሊየሱስ ክርስቶስ ለመነጠል ጥረት ያደርጋሉ /ሮሜ. 8:38/።
3. የቅዱሳን መላእክት ሥራና አገልግሎትን ይቃወማሉ /ዳን. 10:12-13/።
4. ከሰይጣን ዓላማ ጋር ይተባበራሉ። ወይንም ሰይጣን ዓላማውን እንዲፈጽም ይረዳሉ /ማቴ. 25:41፣ ኤፌ. 6:12፣ ራዕ. 12:7-12/።

ለ. የአጋንንት ወይንም የርኩሳን መናፍስት ሥራ

1. በበሽታ ማለቃየት / ኢዮ. 2:5-9፣ ማቴ. 9:33፣ 12:22፣ ሉቃ. 9:37-42፣ 13:11,16/።
2. የሰውን አእምሮ ማቃወስ ማር. 5:4-5፣ ሉቃ. 8:35/። ሁሉም የአእምሮ ሕመም መነሻ ግን አጋንንት ላይሆኑ ይችላሉ። በሌላ ምክንያትም ሊከሰት እንደሚችል መገንዘብ ያለፈልጋል።

3. ብዙዎችን ግብረገብነት ወደ ጐደለው አጸያፊ ድርጊት መምራት /ዘሌ. 18:6-30/።
4. የሐሰት ትምህርትን ማሠራጨት/disseminate false doctrine/ 1ኛ ነገ. 22:21-23፣ 2ኛ ተሰ. 2:2፣ 1ኛ ጢሞ. 4:1/።
5. የእግዚአብሔርን ልጆች መንፈሳዊ እድገት መቃወም /ኤፌ. 6:12/።
6. ከሰዎችም አልፈው በእንስሳት ውስጥ መግባት /ማር. 5:8 14/።
7. የእግዚአብሔር ፈቃድ ይፈጸም ዘንድ መሣሪያ መሆን /መሳ. 9:23፣ 1ኛ ሳሙ. 16:14፣ መዝ. 78:49/። በተለይም በአስከፊው መከራ ጊዜ /ራእይ 9:1-12፣ 16:13-16፣ 2ኛ ተሰ. 2:9/።

ሐ. የሰይጣን ሥራ / The work of satan/

የሰይጣን ስሞች የክፋት ሥራዎቹን የሚገልጹ ናቸው። ስሞቹም የተሰጡት ከሚያደርጋቸው ሥራዎች መነሻነት ነው። ሰምሳሉ «ሰይጣን» የሚሰው ስሙ እግዚአብሔርንና ቅዱሳንን የሚቃወም መሆኑን የሚያመለክት ነው።

- ዲያቢሎስ የሚለው ስሙ ደግሞ የቅዱሳን ከሳሽ እንደሆነ የሚያመለክት ነው /ራእይ 12:10/። ዲያብሎስ የሚለው የግሪክ ቃልም በአዲስ ኪዳን እንጂ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የለም።
- ፈታኝ የሚለው ስሙ ደግሞ ለምችን አባብሎና አታሎ ወደ ኃጢአት የመገፋፋት ድርጊቱን ያመለክታል። ከጠቀስናቸው ሥራዎቹ በተጨማሪ ሌሎችም ክፋ ሥራዎች አሉት።

1. «የሐሰት አባት» እንደመባሉ ወደ ሐሰት ይገፋፋል፤ ሐሰተኛ ያደርጋል /ዮሐ. 8:44፣ 2ቆሮ. 11:3/።
2. የእውነትን ቃል ከሰዎች ልብ ውስጥ ይነጥቃል /ማቴ. 13:19/።
3. ቅዱሳንን ይጎሰማል። ደግሞም ያስፈራራልም /2ኛ ቆሮ. 12:7፣ ኢዮ. 1 እና 2/።
4. ለቅዱሳን እንቅፋት ይሆናል /ዘካ. 3:1፣ 1ኛ ተሰ. 2:18፣ ኤፌ. 6:12/።
5. እምነታቸው እስኪጠፋ ድረስ ቅዱሳንን በፈተና ያበጥራል /ሉቃ. 22:31/።
6. ያልሆነውን ለመምሰል ይሞክራል /2ኛ ቆሮ. 11:14-15፣ ማቴ. 13:25/።
7. በበሽታ ይመታል /ሉቃ 13:16፣ 1ኛ ቆሮ. 5:5/።
8. በሰው ውስጥ ያድራል /ዮሐ. 13:27/
9. ይገድላል /ዮሐ. 8:44፣ 1ኛ ጴጥ. 5:8/

6. የወደቁ መላእክት የመጨረሻ እድል ፋንታቸው

ሀ. በእሳት ባሕር ውስጥ መጣል /ማቴ. 25:41፣ ራእይ 20:1-3፣7-10/

ለ. የቅዱሳንን ፍርድ መቀበል /1ኛ ቆሮ. 6:3/

ክፍል ሁለት

አስተምህሮተ መጽሐፍ ቅዱስ /Doctrine of the Bible/

መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ደራሲነትና በሰዎች ጸሐፊነት የተቀነባበረ መለኮታዊ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ እግዚአብሔር ራሱን በሙላት የገለጠበት የመጨረሻው ልዩ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው። በውስጡም ያለው ዓላማ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያዘጋጀውን የማዳን ፍቅሩን የሚያሳይና ከዘላለም ሞት የሚዋጅበትን አስደናቂ አቅድም የሚገልጽ ነው።

ይህ ታላቅ የእግዚአብሔር ፕሮግራም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተፈፃሚነትን እንደሚያገኝ የሚያረጋግጥ መልዕክትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገባ ተካትቷል። እግዚአብሔርም አስቀድሞ እንደደነገገው ጊዜው ሲደርስ ሁሉም በቅደም ተከተል ከፍፃሜው ደርሷል። ይህን የተዘገበውን እውነት በማንበብና በተለያየ መንገድ በመረዳት ወደ መዳን ይመጡ ዘንድ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን በታሪክ ሂደት ውስጥ ለሰው ልጅ ሰጥቷል።

መጽሐፍ ቅዱስ የማይለወጥ ዘላለማዊ የሆነ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ነው። ስለሆነም መንፈሳዊ ትምህርቶች፣ የእምነት ልምምዶችና መሠረታዊ የሆኑ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ሁሉ የሚለኩበት መለኮታዊ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ ነው። ከዚህም ባሻገር መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወታችን የሚመራበት ብርሃን ነው። ይህን በመገንዘብ በራሳችን ላይ ባለሥልጣን እንዲሆንና እንዲነግሥ ልንፈቅድለት ይገባል።

ምዕራፍ አንድ

1. በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተፃፈ መጽሐፍ /Inspired Book/ የተጠራባቸው ስሞችና ርዕሶች

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ /The Bible/

ቢብሊአስ /Biblios/ የሚለው የግሪክ ቃል መጽሐፍ ማለት ሲሆን ከዚህ ደግሞ "Bible" የሚለው የእንግሊዝኛው ቃል ሊገኝ ችሏል:: "Bible" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በቅዱሳት ጽሑፎች ውስጥ ተጽፎ ባይገኝም "Biblios" የሚለው የግሪኩ ቃል ግን በተደጋጋሚ በመጠቀስ ጥቅም ላይ ውሏል::

መጽሐፍ ቅዱስ የ66 መጻሕፍት ስብስብ የሆነ መለኮታዊ መጽሐፍ ሲሆን የመጽሐፍት ሁሉ የበላይ ነው:: እጅግ ውድ የሆነና ተወዳዳሪም የሌለው ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን እነርሱም ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን በመባል ይታወቃሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ በጽሑፍ የሠፈረ ብቸኛ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃልም ነው::

ለ. የእግዚአብሔር ቃል / The Word of God/

ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በለምኛ ቢሆንም አንዲጽፉ ለለምኛ ትእዛዝ የሰጠው ግን እግዚአብሔር ነው:: በዚህ ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ ከሁለት ሺህ ጊዜ በላይ «የእግዚአብሔር ቃል» በመባል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል:: ቀጥለው ያሉት ስሞችም ለቃሉ-እግዚአብሔር የተሰጡ ናቸው::

1. የእግዚአብሔር ቃል /1ኛ ተሰ. 2:13፣ ዕብ. 4:12፣ ኤፌ. 6:17፣ ማር. 7:13፣ ቆላ. 1:25፣ ዮሐ. 10:35፣ ሉቃ. 8:11/::

2. የጌታ ቃል /ኤር. 1:2,11፣ ሕዝ. 1:3፣ ኢሳ. 1:10፣ ሆሴ 1:1፣ የሐዋ. 8:25፣ 2ኛ ተሰ. 3:1፣ 1ኛ ጴጥ. 1:23-25፣ ኢሳ. 40:8፣ 1ኛ ተሰ. 1:8፣ 4:15፣ የሐዋ. 13:48-49/::
3. የክርስቶስ ቃል /ቆላ. 3:16/::
4. የሕይወት ቃል /ፊል. 2:16/::
5. የእውነት ቃል /ኤፌ. 1:13/::
6. የእምነት ቃል /ሮሜ. 10:8/::
7. ቃል /ያዕ. 1:21-23፣ ዮሐ. 1:1-3፣ ሉቃ. 4:4፣ 1ኛ ጢሞ. 4:5፣ ሮሜ. 10:17፣ የሐዋ. 4:31፣ 6:4/::

ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው ቃል ነው:: ቃልም ሥጋ ሆነ:: መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ የተጻፈ ቃል ነው:: ይሁን እንጂ ሁለቱም የተጻፈው ቃልና ሥጋ የሆነው ቃል በግሪክ /Logos/ በመባል ይጠራሉ:: ሕያው ቃል /ኢየሱስ ክርስቶስ/ በተጻፈው ቃል ውስጥ የተገለጠ ሲሆን የተጻፈው ቃል ደግሞ ወደ ሕያው ቃል /ኢየሱስ ክርስቶስ/ ይመራናል::

ሐ. መጻሕፍት /The Scriptures/

ቅዱስ መጽሐፍ /Scripture/ የሚለው ቃል ጽሑፍ /writing/ ወይንም ጽሑፎች /writings/ ማለት ነው:: የቅዱስ መጽሐፍ /Scripture/ ደራሲ እግዚአብሔር ስለሆነ ለምኛ በራሳቸው ተነሳሽነት ከሚጽፉዋቸው መጻሕፍት ወይንም ጽሑፎች ጋር ሊነጻጸር አይችልም:: ቅዱሳት መጻሕፍት /The Scriptures/ የሚለው ቃል በወንጌላት ውስጥ ከ24 ጊዜ ያላነሰ የተጠቀሰ ሲሆን በሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ደግሞ ለ28 ጊዜ ተጠቅሷል:: እጥቅም ላይ ውሏል:: በብሉይ ኪዳን ውስጥ ግን

ተጠቅሶ የምናገኘው አንዱ ብቻ ነው። እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍትም ቀጥሎው ባሉት ስሞች ተጠርተዋል።

1. የእውነት መጽሐፍ /ዳን. 10:21/

2. መጽሐፍ /ማር. 12:10፣ 15:28፣ ሉቃ. 4:21፣ ዮሐ. 2:22፣ 7:38፣ 10:35፣ ሮሜ 4:3፣ 2ኛ ጢሞ. 3:16፣ ገላ. 3:8፣ 22 4:30፣ የሐዋ. 1:1, 6፣ ዮሐ. 19:24, 28, 36-37፣ 20:9/።

3. መጻሕፍት /ማቴ. 21:31፣ 22:29፣ 26:54,56፣ ማር. 12:24፣ ሉቃ. 24:27፣ ዮሐ 5:30፣ ሮሜ. 16:26 የሐዋ. 13:27፣ 17:11፣ 2ኛ ጢሞ. 3:15፣ 1ኛ ቆሮ. 15:3፣ ዮሐ. 7:38, 42፣ ሮሜ. 1:2፣ 2ኛ ጴጥ. 3:16/

4. ቅዱሳት መጻሕፍት /2ኛ ጢሞ. 3:15፣ ሮሜ. 1:2/

መ. የእግዚአብሔር ንግግሮች /ቃል/ እግዚአብሔር ንግግሮቹን /ቃሉን/ የሚናገርበት ቦታ /The Oracles of God/

"Oracle" የሚለው ቃል፣ ቃል በቃል ሲተረጎም የንግግር ቦታ /The Speaking Place/ ማለት ነው። ክርስትና ዝም በማይል፣ ነገር ግን በሚናገር በላለማዊ አምላክ በማመን የተመሠረተ እምነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በርግጥም የእግዚአብሔር ንግግር /ቃል/ ነው። ደግሞም እግዚአብሔር የሚናገርበት ቦታም ነው። ሕግም ቢሆን ወደ እግዚአብሔር ሕያው ንግግሮች /ቃል/ የሚያመለክት ነው /ሮሜ. 3/።

በቤተመቅደስም በቅድስና የላቀው ሥፍራ የተቀደስ የንግግር ቦታ /The Holy Oracle/ በመባል ይጠራል። ሥፍራው የእግዚአብሔር ማደሪያ ሥፍራ ስለሆነ ቅድስተ ቅዱሳን ነው /Most Holy Place/። እግዚአብሔርም ከዚህ ሥፍራ ሆኖ ይናገር ነበር፦ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ «ሳሙኤልም ደግሞ

የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ ተኝቶ ነበር... እግዚአብሔርም መጥቶ በዚያ ቆመ፣ ቀደም ሲል እንዳደረገው ሁሉ ሳሙኤል ሳሙኤል ብሎ ጠራው። ሳሙኤልም፣ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር አለ» /1ኛ ሳሙ. 3:3-10/። እንግዲህ ይህ ቅዱስ የእግዚአብሔር ማደሪያ ሥፍራ እግዚአብሔር የሚናገርበት ቦታ ስለሆነ ከዚህ የተነሳ የተቀደስ የንግግር ቦታ /The Holy Oracle/ ተብሎ ይጠራል።

ሠ. ብሉይና አዲስ ኪዳናት

"Testament" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል «ቃል ኪዳን» /Covenant/ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም በሁለት ኪዳናት የተከፈለ ነው። እነርሱም 1. የሕግ ኪዳን /The Convenant of Law/ ወይንም ብሉይ ኪዳን /The Old Testament/ 2. የፀጋ/አዲስ ኪዳን /The New Testament/ ናቸው። ዘጠኝ ያህል መለኮታዊ ኪዳናት እንዳሉ ቢታወቅም እግዚአብሔር ግን ከሰው ጋር ግንኙነት ያደረገው ሁለቱን ኪዳናት መሠረት በማድረግ ነው።

ከላይ እንደተገለጠው ብሉይ ኪዳን በሙሴ ·በኩል የተሰጠውን ሕግ መሠረት በማድረግ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚያመለክት ነው። አዲስ ኪዳን ደግሞ በኢየሱስ በኩል የተሰጠውን ፀጋ መሠረት በማድረግ እግዚአብሔር ከዓለም ጋር ያደረገውን ግንኙነት የሚያንፀባርቅ ነው።

ኤርምያስ ገና በእሮጌው ኪዳን ሥርዓት ሳለ ሊመጣ ስላለው አዲስ ኪዳን ተነበየ /ኤር. 31:31-34 በተጨማሪ ዕብ. 8:6-13፣ 10:15-17/። እስቀድሞ እንደተተነበየ ሁሉ ኢየሱስ አዲስ ኪዳንን በመመሥረት እሮጌው ከፍጻሜ እንዲደርስ አደረገ

/ሉቃ. 22:20፣ 1ቆሮ. 11:25፣ ማር. 14:24፣ ማቴ. 26:26-28፣ ዕብ. 9:15፣ 12:24፣ 2ኛ ቆሮ. 3:6,14፣ ማቴ. 5:17-18፣ 11:13፣ ሮሜ. 3:21/። ከዚህ በኋላ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የተጠራባቸውን ተምሳሌቶች እንመለከታለን።

2. በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተፃፈ መጽሐፍ /Inspired Book/

ተምሳሌቶች

ሀ. እሳት /ኤር. 23:29/

- የቅድስና ተቃራኒ የሆነውን ሁሉ ያቃጥላል፣ ያጸዳል፣ ይጠርጋልም።

ሰ. መዶሻ /ኤር. 23:29/

- ክፋትን ይሰብራል፣ ያጠፋልም።

ሐ. ብርሃን/መብራት /መዝ. 119:105/

- ጨለማን የሚያበራ ትልቅ መሣሪያ ነው።

መ. መስተዋት /ዕብ. 1:23/

- ከእግዚአብሔር ጋር ስንኖር እውነተኛ ማንነታችንንና መሆን ያለብንን ያሳየናል።

ሠ. ወተት /1ኛ ጴጥ. 2:2/

- በክርስቶስ አዲስ ለሆኑት ምግብ በመሆን ያሳድጋል።

ረ. መስኪያ /ራእይ 11:1-2/

- ከእምነትና ከልምምድ ጋር ስተያያዙ ነገሮች ሁሉ መለኮታዊ የሆነ መስኪያ ነው።

ሰ. ዘር /1ኛ ጴጥ. 1:23፣ ሉቃ. 8:11፣ ያዕ. 1:18/

- ይበቅላል፣ ሕይወትን ያፈራል፣ ማደግ የሚችለውን የዘላለም ሕይወትንም በውስጡ ይዟል።

ሸ. ሰይፍ /ዕብ. 4:12/

- የተሳለና በሁለቱም በኩል የሚሠራ ነው። የሥጋንና የመንፈስን ነገሮች ሁሉ ይለያያል።

ቀ. ውኃ /ኤፌ. 5 5:26፣ ዮሐ. 15:3፣ 17:17፣ መዝ. 119:5,9/

- ሕይወት ሰጪ ነው። ያድሳል፣ ያነጻል፣ ይለውጣልም።

በ. ወርቅ /መዝ. 19:7-10፣ ኢዮ. 28:1፣ ምሳ. 25:2/

- ሊገመት የማይቻልና እጅግ ውድ የሆነ ዋጋ ያለው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ማንም ቆፍሮ የማይጨርሰው የወርቅ ማዕድንና የዘላለም ሀብት ነው።

ተ. ማር. /መዝ. 19:10፣ ራእይ 10:10/።

- ጣፋጭ ጣዕም ያለው ነው። የእግዚአብሔርም ቃል እንደ ማር የጣፈጠ የነፍስ ምግብ ነው።

ቸ. ችንክር /መክ. 12:11/።

- በሬ ወይም ፈረስ በተወሰነ የግጦሽ ስፍራ ተመሽገው እንዲቆዩ ስማድረግ በመሬት ተቸንክሮ ገመዳቸው የሚታሰርበት ሹል እንጨት፡ ልክ እንደዚሁ የእግዚአብሔርም ቃል ሰሰምች ከመቅበዝበዝ አርፈው በእግዚአብሔር አረኝነትና ጥበቃ ሥር እንዲቆዩ ያደርጋል።

ኀ. እንጀራ /ማቴ. 4:4፣ ዘዳ 8:3፣ መዝ. 119:103፣ ኢሳ. 55:10፣ ዘፀ.16/

- የሕይወት ምርኩዝ ነው። ሁሉ አዲስ፣ መልካም የሆነ የየዕለት ፍጆታ ነው።

ነ. ዕንቁ /ማቴ. 7:6/

- ውድና የከበረ ድንጋይ ነው። እንዲሁ ሲታይ ድምቀት ባይኖረውም ወደ ብርሃን ወጥቶ በብርሃን ሲታይ ግን በርካታ ሕብረ ቀለማትን የሚፈነጥቅ እጅግ የቆነጀና

የሚያምር ደግሞም የሚያለምር ክቡር ድንጋይ ነው። የእግዚአብሔርም ቃል ደግሞ እንዲሁ የከበረ፣ ውድ የሆነ፣ የሰውን ሕይወት የሚያለምርና ፈርጀ ብዙ መልዕክት ያለው ልዩ ዕንቁ ነው።

ኘ. መልሕቅ /ዕብ. 6:18-19/

- መልሕቅ መርከብ ስማዕበልና ወጀብ እንዳይናወጥ እንደሚያጸናው ሁሉ የእግዚአብሔርም ቃል በማንኛውም ማዕበል ውስጥ የአማኝ ደህንነት ዋስትና ነው።

አ. ከክብ /2ኛ ጴጥ. 1:19፣ ራእይ 2:28/

- አማኝን ወደ ክርስቶስ ይመራል።

ክ. ምግብ /ዕብ. 5:14/

- ለሰውነት ብርታትን የሚሰጥ የኃይል ምንጭ ነው። የእግዚአብሔር ቃልም በአማኞች ሕይወት ተመሳሳይ ሥራን ይፈጽማል።

3. መጽሐፍ ቅዱስ የሚከፋፈልባቸው ልዩ ልዩ መንገዶች

መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ላይ ተጠርዞ ሲታይ አንድ መጽሐፍ ቢመስልም በውስጡ ግን 66 መጻሕፍትን ያካተተ ነው። እነዚህም መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱስን በተለያዩ መንገዶች እንዲከፋፈል ያስችሉታል። በዚህ መሠረትም መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ በምዕራፎችና እንዲሁም ደግሞ በቁጥሮች ሥር የተከፋፈለ ነው።

ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 39 ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት ደግሞ ቀጥለው ባሉት ክፍሎች ይከፈላሉ።

1. የታሪክ መጻሕፍት /ከዘፍጥረት እስከ አስቴር/

2. የቅኔ ወይንም የጥበብ መጻሕፍት /ከኢዮብ እስከ መኃልይ ዘሰለሞን

3. የትንቢት መጻሕፍት /ከኢሳያስ እስከ ሚልክያስ/ በመባል ይከፈላሉ።

ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ደግሞ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ቀጥሰው ባሉት መንገዶች ይከፋፍሉአቸዋል።

1. 5ቱ የሕግ መጻሕፍት - { ዘፍጥረት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘጎልቁ፣ ዘዳግም

2. ነቢያት
   - { ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሣሙኤል፣ ነገሥት፣
   - { ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል /ታላላቅ ነቢያት/
   - { አሞጽ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ሚክያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስ፣

3. ጽሑፎች /Holy Writings/ - መዝሙረ ዳዊት፣ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ ሩት፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፣ መክብብ፣ ለቆቃወ ኤርምያስ፣ አስቴር፣ ዳንኤል፣ ዕዝራ፣ ነህምያና ዜና መዋዕል በማለት ይከፋፍሉአቸዋል።

ለ. አዲስ ኪዳን

- አዲስ ኪዳን በሶስት ክፍሎች ይከፈላል። እነዚህም፦

1. ታሪካዊ መጻሕፍት /ወንጌላትና የሐዋርያት ሥራ/
2. መልዕክቶች
3. ራእይ ናቸው።

ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ በምዕራፍ መከፋፈል

መጽሐፍ ቅዱስ በምዕራፍና በቁጥሮች የመከፋፈሉ ጉዳይ ከጥንት በነበሩት ጽሑፎች ላይ ያልተደረገ አዲስ ክስተት ነው። ስለሆነም ሰዎች ምቹ የሆነ የአጠቃቀም ሁኔታን ለመፍጠር ሲሉ ከዘመናት በኋላ ያመጡት የአከፋፈል ስልት ነው። የጥንት አይሁዳውያንም ብሉይ ኪዳንን በተሰያዩ ክፍሎች በመከፋፈልና በምኩራቦቻቸው በመጠቀም በጊዜ ሂደት ስመጣው የመጽሐፍ ቅዱስ አከፋፈል ዘዴ መሠረት ሆነዋል። ስለሆነም ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምንመለከተውን የጥቅስ አከፋፈል ዘይቤን ያመነጩት ማሶሬትስ የተባሉ የአይሁድ ምሁራን ነበሩ። ጊዜው በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አንደሆነ ይታመናል።

ከዚህ በኋላ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የታየው አዲስ ነገር ደግሞ ዘመናዊነትን በተላበሰ መልኩ በምዕራፍ የመከፋፈሉ ጉዳይ ነው። ይህንንም አከፋፈል ያመጣው ካርዲናል ሁጎ /Cardinal Hugo/ የተባለው ስው ነው። ጊዜውም በ13ኛው ክፍለ ዘመን አንደነበር የብዙዎች አምነት ነው። ካርዲናል ሁጎም ከዚህ አስተዋጽኦው በኋላ በ1263 መሞቱ ታውቋል። ከዚህ በኋላ ደግሞ አስቴፈንስ /Stephens/ የተባለ ስው በ1551 ዓ.ም አዲስ ኪዳንን በጥቅስ ከፋፈለ። ከፍፍሉ እንከን የለሽ ባይሆንም ጥቅሙ ግን ጥያቄ የሌለው ነው። በዚህ መልኩ የተከፋፈለውን መጽሐፍ ቅዱስ አንዲፃፍ ያዘዘው እግዚአብሔር ነው። ይህ ቀጥለን የምንመለከተው ነጥባችን ይሆናል።

4. መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የተፃፈ ነው

መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለመጻፉ በቂ የሆነ ማስረጃን ይሰጣል። ቀጥለው የተፃፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይህንኑ እውነት የሚያረጋግጡ ናቸው።

ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን፣ «ሲታወስ እንዲኖር ይህን በጥቅልል መጽሐፍ ላይ ጻፈው፤ ኢያሱም መስማቱን እረጋግጥ፤ ምክንያቱም የአማሌቃውያንን ዝክር ከሰማይ በታች ፈጽሜ እንደመስሳለሁ» አለው። (ዘጸ 17:14)

ኢያሱም እነዚህን ቃሎች በእግዚአብሔር የሕግ መጽሐፍ ጻፋቸው። ትልቅ ድንጋይም ወስዶ በባሉጥ ዛፍ፣ ሥር በተቀደሰው በእግዚአብሔር ሥፍራ አጠገብ አቆመው። (ኢያሱ 24:26)

አሁንም ሂድ በስሌዳ ላይ ጻፍላቸው። በጥቅልል ጽሑፍ ላይ ከተብላቸው። ለሚመጡትም ዘመናት ስዘላለም ምስክር ይሆናል። (ኢሳ. 30:8)

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የነገርሁህን ቃል ሁሉ በመጽሐፍ ጻፈው። (ኤር. 30:2)

አብ በስሜ የሚልከው አጽናኝ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል። (ዮሐ. 14:26)

ማንም ነቢይ ነኝ የሚል፣ ወይንም መንፈሳዊ ስጦታ አለኝ የሚል ቢኖር ይህ የጻፍሁላችሁ የጌታ ትዕዛዝ መሆኑን ይወቅ። (1ኛ ቆሮ. 14:37)

ደግሞም ቀድሞ በቅዱሳን ነቢያት የተነገረውን ቃል እንዲሁም ቤሐዋርያታችሁ አማካይነት በጌታችንና በአዳኛችን የተሰጠውን ትዕዛዝ እንድታስቡ ነው። (2ኛ ጴጥ. 3:2)

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንደተጻፈ ስለ ራሱ የሰጠውን በቂ ማስረጃ ከላይ ተመልክተናል። የተጻፈውም በእግዚአብሔር ደራሲነትና ከ40 በላይ በሚሆኑ ሰዎች ጸሐፊነት ነው። እነዚህ ሰዎች ትዕዛዙን ከእግዚአብሔር በመቀበልና በመንፈሱ ሥልጣን ሥር በመሆን መጽሐፍ ቅዱስን ጽፈውታል። መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ለማለቅ ከ1500 ዓመታት በላይ እንደፈጀ ይታመናል። ተጽፎ ያለቀውም ከዛሬ 1900 ዓመታት በፊት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንድ መጽሐፍ መከሉ ቢታይም በውስጡ ግን 66 መጻሕፍትን ያካተተ ነው። የእነዚህ መጻሕፍት ጥምር አንድነትም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲባል አስችሎታል። ምዕራፎቹ 1188 ሲሆኑ ከ1500 ቋንቋዎች በላይ በመተርጎም ተወዳዳሪ የሌለው ብቸኛ መጽሐፍ ነው። ከማናቸውም መጻሕፍት በፊት በመታተምም እንጋፋነቱን ያረጋገጠ ነው። እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ እስደናቂና ተአምራዊ ነው የሚያስኙት ነጥቦች፡

1. ከ1500 ዓመታት በላይ በሆነ ጊዜ በተለያየ ጊዜ መጻፉ
2. ጸሐፊዎቹ ግንኙነት ላይኖራቸው እንድ ወጥ የሆነ መጽሐፍ መጻፋቸው
3. መንፈስ ቅዱስ ከጸሐፊዎቹ በላይ ሆኖ መምራቱ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከ40 በሚበልጡ በተለያዩ ሰዎች ቢጻፍም እንኳ መልእክቱ ወጥ መሆኑ ምንጩ እግዚአብሔር ስመሆኑ ተጨማሪ ማስረጃ ነው። እነዚህ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች በተለያየ ጊዜ የኖሩና የተለያየ ሥራም የነበራቸው ነበሩ። ለምሳሌ፡

- ሙሴና ኢያሱ መሪዎች ነበሩ /ዘጸ. 3:10፣ ኢያ. 1:1-5/።
- ዳዊት የበግ አረኛ ነበር፣ በኋላ ግን የእስራኤል ንጉሥ ሆነ /1ኛ ሳሙ. 17:15,20፣ 34-35/።

- እሞጽ የላምና የበግ ጠባቂ፣ የዋርካ ለቃሚም ነበር /እሞ. 1:1፣ 7:14/።
- ዳንኤል የመንግሥት ባለሥልጣን ነበር /ዳን. 6:1-3,28/።
- ማቴዎስ ቀራጭ ነበረ /ማቴ. 9:9/።
- ሉቃስ ሐኪም ነበረ /ቆላ. 4:14/።
- ጴጥሮስ ዓሣ አጥማጅ ነበረ /ማር. 1:16-17/።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በተለያዩ ቦታዎችና ሁኔታዎች ውስጥ የተጻፈ ነው። ለምሳሌ፡-

- ሙሴ በበረሃ ጽፎታል።
- ዳዊት በገጠር የበግ አረኛ ከነበረበት ጊዜ እንስቶ፣ ሳኦል ቤተ መንግሥት በኋላም በራሱ ቤተ መንግሥት ሆኖ መዝሙሮቹን ጽፏል።
- ለሰሞን ምሳሌዎቹን በነገሥታት ግቢ ውስጥ ስተባቸው።
- ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ታስሮ ሳለ የዘመናትን እፈጻጸም ራእይ ተቀበለ።
- ጳውሎስ በወህኒ ቤት ውስጥ ሆኖ አምበቱን መልእክቶች ጽፏል /ኤፌሶን፣ ፊልጵስዩስ፣ ቆላስይስ፣ ፊልሞና፣ 1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ/።

መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈባቸው ቦታዎች

- በአውሮፓ /ጳውሎስ በሮም አሥር ቤትና በቆሮንቶስ ሆኖ ሲጽፍ አውሮፓ መሆኑ ነው/።
- በአፍሪካ /ሙሴና ኤርምያስ/
- በእስያ /አብዛኛዎቹ መጻሕፍት የተጻፉበት አህጉር ነው/

ለማጠቃለል መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ□ በተማሩና ባልተማሩ፣ በአይሁድና በአሕዛብ ተሳትፎ የተጻፈ ነው። ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ጸሐፊዎች እርስ በርስ የሚተዋወቁ አልነበሩም። ከዚህ አኗያ የሚያስደንቀው ነገር መልዕክቱ አንድ ወጥ መሆኑና እግዚአብሔር ስውን ስማዳን ያቀደውን ዓላማ በሚያስገርም ሁኔታ አስረግጦ መናገሩ ነው። ጸሐፊዎቹም ግማሾቹ ከጌታ ልደት በፊት፣ ግማሾቹ ደግሞ በምድር አገልግሎቱ ዘመን የነበሩና ሌሎቹም ከእርገቱ በኋላ ነው መጽሐፉን የጻፉት። ቀደም ሲል እንደተባለው ጸሐፊዎቹ መጽሐፉን ወደ መጻፍ ያመሩት በራሳቸው ሳይሆን በእግዚአብሔር ትዕዛዝና /ዘጸ. 17:14፣ ኢያ. 24:26/ በመንፈሱ አነሳሽነት ነው /2ኛ ጴጥ. 1:21/።

5. መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት የሚለይባቸው መንገዶች

ሀ. በሰነ ጽሁፉ ልዩ መሆን /Literary Uniqueness/

1. ከ1500 ዓመታት ስላይ በፈጀ ጊዜ ውስጥ በመፃፉ
2. በ60 ትውልድ በመፃፉ
3. ከ 40 ፀሐፊዎች በላይ የተሳተፉበት መሆኑ
4. በሦስት አህጉራት የተጻፈ በመሆኑ /አስያ፣ አፍሪካ፣ አውሮፓ/
5. በሦስት ቋንቋዎች በመጻፉ ምክንያት /ዕብራይስጥ፣ አራማይክና ግሪክ/

ለ. ይቅርታንና ምህረትን በሚመለከት የተለየ በመሆኑ

- እግዚአብሔር ይቅር ባይና መሃሪ አምላክ መሆኑን የሚነግረን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው።

ሐ. በትንቢቶቹ መፈጸም በኩልም የተለየ ነው

የተፈጸሙ ትንቢቶች የሚገኙበት ብቸኛ መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። በውስጡም ከ3800 በላይ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» የሚል ትንቢታዊ የሆነ ሐረግ ተጽፎ እናገኛ ለን። በዚህም መሠረት፦

1. ነቢዩ ሕዝቅኤል በ592 ከክርስቶስ ልደት በፊት የጢሮስን ከተማ መደምሰስ አስመልክቶ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብሎ ንግግሩን እንደጀመረ ተጽፏል /ሕዝ. 26/። ሕዝቅኤል ትንቢታዊ ቃልን ያስተላልፍ እንጂ ተናጋሪው እግዚአብሔር ነው። ጢሮስ በታላቁ ባሕር ዳር የነበረች የፊንቄ ጥንታዊት ከተማ ስትሆን የተቆረቆረችውም በሲዶና ሰዎች ነው። እንደተጠቀሰው በ597 ከወገኖቹ ጋር ወደ ባቢሎን የተማረከው ነቢዩ ሕዝቅኤል ስሰዚች ከተማ አስመልክቶ ቀጥሰው ያሉትን ትንቢቶች ተናግሮ ነበር /ሕዝ. 26:4-14/።

   ሀ. ጢሮስ እንደበትደመሰስ

   ለ. ዳግመኛ እንደማትሠራ

   ሐ. የመረብ ማስጫ ቦታ እንደምትሆንና የተራቆተ ከፍታም እንደምትሆን ተናገረ።

=> በኢንሳይክሎፒዲያ ላይ ሰንመለከት

ሀ. ጢሮስ በ585 ከክርስቶስ ልደት በፊት ትንቢቱ ከተነገረ ከሰባት ዓመታት በኋላ ተደምስሳለች።

ለ. ዳግመኛ አልተሠራችም /ታላቁ አሌክሳንደር በ332 ሊሠራት ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቷል/።

- እንደ ተተነበየባትም የመረብ ማስጫ ሆናለች። ይህን ክፍል እንደ ምሳሌ ወስድን እንጂ ብዙ የተፈጸሙ ትንቢቶችን በመያዙ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት የተለየ መሆኑን አስመስክሯል።

2. ኢየሱስን በተመለከተ

- በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ወደ 332 ትንቢቶች መሲሁን አስመልክቶ ተነግረዋል። ስለ መሲሁ የተነገሩት ትንቢቶች ሁሉ ጊዜው ሲደርስ በኢየሱስ ሕይወት ተፈጽመዋል። ለምሳሌ፤
  - ክዳዊት ወገን መሆኑ /ኢሳ. 11:1፤ ማቴ. 1:11/፤
  - በቤተልሔም መወለዱ /ሚክ. 5:2፤ ሉቃ. 2:11/፤
  - ክድንግል መወለዱ /ኢሳ. 7:14፤ ማቴ. 1:23፤ ሉቃ. 2:11/፤
  - በ30 ብር /Silver/ መሸጡ /ዘካ. 11:12፤ ማቴ. 26:15/፤
  - በሁለት ሌቦች መካከል መሰቀሉ /ኢሳ. 53:9,12፤ ዮሐ. 19:18/፤
  - ከመታን ተሰይቶ መነሳቱና ሌሎችም ተፈጽመዋል /ኢሳ. 53:9፤ ማቴ. 27:50፤ 28:5-6/።

ምዕራፍ ሁለት

1. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዓላማ

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ ሲፈቅድና ትእዛዙን ሲያስተላልፍ ግልጽ ከሆነ ዓላማ ጋር ነበር። ዓላማውም ራሱን በሙላት በመግለጥ ለዎች እርሱን ያውቁ ዘንድ መርዳት ነው። ከዚህ በመነሣት መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈው ለሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰውን መንገድ ለማሳየት ነው ማለት እንችላለን። ይህም መንገድ የደህንነት መንገድ ሲሆን እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው /ዮሐ. 14:6/። በኋላም ሐዋርያው ጳውሎስ በጌታ ልጁ ለሆነው ጢሞቴዎስ መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ዓላማ እንደተፃፈ በ2ኛ ጢሞ. 3:14-17 ባለው ክፍል ውስጥ ጽፎለታል። በጥቅሱ መሠረትም ሐዋርያው ጳውሎስ መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈበትን ዓላማ ቀጥሎ ባለው መልክ ከፋፍሎ አስቀምጦታል።

ሀ. ለዎች በክርስቶስ በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ማግኘት እንዲችሉ ነው ይላል። ይህም ጥበብ ሌላ ሳይሆን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በማለት ያረጋግጣል /1ኛ ቆሮ. 1:24/።

ለ. የእግዚአብሔር ስው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ እንዲሆን ለማስቻል ነው ሲል ጠቅለሎታል።

2. ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እንዴት እናውቃለን ?

ቀጥለው ያሉት ሦስት ማስረጃዎች ምላሽ የሚሰጡ ናቸው።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ለለ ራሱ በቂ የሆነ ምስክርነትን በመስጠቱ

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ለለራሱ መመስከሩ በራሱ ብቁና ማንም ሊቀበለው የሚገባ ሥልጣናዊ ቃል ነው /2ኛ ጢሞ. 3:15-17፤ 1ኛ ጴጥ. 1:21/። ይህ ማለት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሌላ ተናጋሪ የለም ማለት አይደለም። ምክንያቱም የሰዎች፣ የመላእክትና የእንስሳት ቃልም አለና ነው። ይሁን እንጂ ቃሉ ስሕተትን ሊያስከትል ከሚችል ከማንኛውም ዓይነት ሁኔታ ተጠብቆ በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት እውነተኛውን ነገር ብቻ እንዲጽፉ ሰዎች በእግዚአብሔር ተመርተዋል። በዚህም መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል የያዘ መጽሐፍ ሳይሆን ራሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው /1ቆሮ. 2:13፣ 2ጴጥ. 3:2/።

ሰ. ጌታ ኢየሱስ በሰጠው ምስክርነት አማካይነት

ጌታ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእግዚአብሔርን ሥልጣን የያዙ መሆናቸውን በልዩ ልዩ መንገዶች ገልጿል /ማቴ. 5:17-19/። በምድር አገልግሎቱ ጊዜም ከሕግ፣ ከነብያትና ከሌሎችም መጻሕፍት በመጥቀስ አስተምሯል። የእነዚህንም መጻሕፍት መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጓል /ማቴ.15:1-9/። የራሱም ቃል መለኮታዊ ሥልጣን ያለው መሆኑንም አረጋግጧል /ዮሐ. 4:46-54፣ ዮሐ. 6:63/። ከዚህ የምንረዳው ብሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆን አዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ነው።

ሐ. ሐዋርያት መጽሐፍ ቅዱስን አስመልክተው ከሰጡት ምስክርነት

ሐዋርያትም በአገልግሎት ዘመናቸው ለመጽሐፍ ቅዱስ የሰጡት ሥልጣን ኢየሱስ ከሰጠው ሥልጣን ጋር የሚመሳሰል እንጂ የሚቃረን አልነበረም። ሐዋርያት አምነታቸውን ለሌሎች በሚያካፍሉበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ይጠቅሱ ነበር /የሐዋ. 1:15-22፣ 4:23-26፣ 28:23-27/። ሌሎች አዲስ ኪዳንን የጻፉ ጸሐፊዎችም እምነታቸው ከብሉይ ኪዳን ጋር የተያያዘ መሆኑን ለማመልከት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በመጥቀስ በጽሑፋቸው ውስጥ ማካተታቸውን መመልከት ይቻላል።

ሐዋርያት የራሳቸውና የሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ጽሑፎች እንደ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሥልጣን እንዳላቸው አረጋግጠዋል /2ኛ ጴጥ. 3:15- 16/። በተጨማሪም 2ኛ ጴጥ. 3:2 የሌሎች ሐዋርያት ጽሑፎች የጴጥሮስንም ጨምሮ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን እንደያዙ ያረጋግጣል።

በይሁዳ 17 ላይ ይሁዳ የሐዋርያትን፣ በ1ኛ ቆሮ. 11:23 ላይ ደግሞ ጳውሎስ የጌታን ትእዛዝ እንደጻፈ ይናገራል። እነዚህ ሦስቱ ጣምራ ምስክርነቶች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አበክረው ያረጋግጣሉ። ስለሆነም ለዚህ ባለሥልጣን ለሆነ ሕያው ቃል ልንገዛና በሕይወታችንም ላይ የበላይ አድርገን ልናነግሠው የሚገባ ነው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ይህን የሥልጣን ቃል የሚገዳደሩትን ተግዳሮቶች እንመለከታለን።

3. የመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣንና ተግዳሮቶቹ

ቀደም ባሉት ዘመናት መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ ታውቆ ተቀባይነት ነበረው። የሚያላዝነው ግን አንዳንዶች ይህን እውነት ይዞ መቀጠል እያቃታቸው መጥቷል። ለዚህ ምክንያት የሆነው የቃሉ እውነተኛ ያለመሆን ሳይሆን የሰዎች በእውነተኛውና ባለሥልጣን በሆነው አምላካዊ ቃል ላይ በተግዳሮት መነሣት ነው። የቃሉ ሥልጣንና እውነተኝነት መፈታተንንም ከብልጣንትና ከጉብዝና ይቆጥሩታል። ሌሎች ደግሞ በቃላቸው እያሞጋገሱ እንደ አስገራሚ መጽሐፍ ይመለከቱታል። ይሁን እንጂ ለሥልጣኑ መገዛትን አይፈልጉም። የእግዚአብሔርን ሕልውና የማይቀበሉ ለዎችም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ «በአክብሮት» ሲናገሩ «መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት ይልቅ በሥነ ጽሑፍ የላቀ ነው» ብለው ብቻ ይደመድማሉ።

ወደ አማኒያኑ ወገን ስንመለስ ደግሞ አንዳንዶቹ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋናና የመጨረሻው ከፍተኛ ባለሥልጣን እንደሆነ ቢቀበሉትም

ስለእርሱ ስሚተርከው የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን መገዛት ግን አይሆንላቸውም። ዛሬ እናት ሳንሄድ እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ በአቅራቢያችን ካሉ አማኞች አካባቢ በቀላሉ ማየት እንችላለን።

እኛ አማኞች አንድ መሠረታዊ እውነት ማወቅ አለብን። ይኸውም የበላይ ባለሥልጣን አድርገን እያንዳንዳችን የተቀበልነው ኢየሱስ «የመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ» መሆኑን ነው። በሰዚህ የኢየሱስን ባለሥልጣንነት በእርግጥ ተቀብለን ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስንም የበላይነትና ሥልጣኑን በመቀበል ለሥልጣኑ ተገዥነታችንን በተግባር ማሳየት ይኖርብናል።

ኢየሱስን ታሪኩን ከሚያወራለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ገንጥለን ማየት አንችልም። ምክንያቱም እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና፦ «እነዚህ መጻሕፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው» /ዮሐ. 5:39/ ስለዚህ ኢየሱስን የተቀበለ ቃሉንም መቀበል ይጠበቅበታል። ቃሉን ተቀብያለሁ ባዩም ደግሞ ኢየሱስን እንዲቀበል ይህ እውነት ግድ ይለዋል። ሁለቱ አይነጣጠሉምና /ዮሐ. 14:23/። ይሁን እንጂ አንዳንዶች የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የመጨረሻው ሥልጣን መሆኑን አይበቀሉም። ምክንያታቸውም እንደሚከተለው ነው።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስና ሳይንስ አይስማሙም ብለው ያምናሉ

በርግጥ ብዙ ያልተረጋገጡና ሳይንሳዊ ያልሆኑ ጽንሰ ሐሳቦች /theories/ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይስማሙም። ነገር ግን እውተኛው ሳይንስና መጽሐፍ ቅዱስ ያልተስማሙበት ወይንም የተጋጨበት ጊዜ ታይቶም አይታወቅም /1ኛ ጢሞ. 6:20/።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስና የከርስ ምድር (አርኪዮሎጂ) /የሥነ ምድር ጥናት ውጤቶች አማይስማሙም ብለው ያምናሉ።

ነገር ግን የከርስ ምድር ጥናት ምሁር የሆኑት ጂኦሎጂስት ጉዮት /Geologist Guyot/ እውነተኛ የሆነ የከርስ ምድር ጥናት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በትክክል እንደሚስማሙ አረጋግጧል።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስና አጠቃላይ የሆነ ሳይንስ /General Science/ አማይስማሙም ብለው ያምናሉ።

ነገር ግን ስቶክስ /Stokes/ የተባለ ሰው ይህ አመለካከት ፈጽሞ ሐሰት እንደሆነ አስረድተዋል።

መ. መጽሐፍ ቅዱስና ኬሚስትሪ /Chemistry/ እንደማይስማሙ ስለሚያስቡ ነው

ይህን በተመለከተ ደግሞ ኬሚስት ራዳር /Chemist Radar/ የተባለው ታላቁ የአሜሪካን ኬሚስት /a Great American Chemist/ ይህ ጉዳይ ፈጽሞ ስህተት መሆኑን አስረድተዋል።

ሠ. አንዳንዶች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስና ሥነ መልክአ ምድር /Geography/ አይስማሙም ብለው ያምናሉ

ዶክተር ክርስቲያይ የሥነ መልክአ ምድር ጠበብት /Dr. Christie, an Eminent Geographer/ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም የሥነ መልክአ ምድር ስህተት እንደሌለ በግልጽ አውጀአል።

ረ. አንዳንዶች ደግሞ የመጨረሻው ባለሥልጣን መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ቤተክርስቲያን ናት ብለው ስለሚያስቡ ነው

በእርግጥ ቤተክርስቲያን አዲስ ኪዳን ከመጻፉ ቀደም ብላ ተመሥርታለች። ይህ ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከቤተ

ክርስቲያን ያነሰ ስልጣን አለው ከሚል ድምዳሜ የሚያደርስ እይደለም። እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን መሠረቷና መመሪያዋ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህን እመለካከት የምታራምደው ለጳጳሶችዋ ፍጹም ሥልጣንን የምትሰጠው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት እንጂ የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እምነት እይደለም።

ስ. ከላይ የተጠቀሱት ተቃውሞዎች የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች

እይሁዶች በጳውሎስ ላይ ያቀረቡትን የክስ ምክንያት የእካይያ ገዥ የነበረው ጋልዮስ በዳኝነቱ መርምሮት ከምንም የማይቆጠር ሆኖ እንዳገኘው ዓይነት ናቸው። በመሆኑም ጋልዮስ በዳኝነቱ እይታ ጳውሎስን የሚያስከስስ በቂ ምክንያት እንደእጣና /የሐዋ. 18:17/ ከወንጀሉ ንጹህ ሆኖ እንዳገኘው ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስም የመጨረሻ ባለሥልጣን እንደሆነ እድርገው ሳለመቀበል ብዙዎች ሥልጣኑን በጥያቄ ውስጥ ለመክተት ካቀረቡአቸው ምክንያቶች ሁሉ የነፃና የጸዳ ነው። ዛሬም ቢሆን ከታሪክ በመማር የጳውሎስ ከሳሾች በሸረቡት ምክንያት የለሽ ክስ መልስው በራሳቸው ላይ ችግርን እንዳስከተሉ ሁሉ እኛም የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን በመገዳደር ልንወጣው ከማንችለው መንፈሳዊ ቀውስ ውስጥ ራሳችንን እንዳንከት ለሥልጣኑ በመገዛት በጥንቃቄ እንመላለስ።

4. የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የበላይነት

ቀደም ሲል የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን የሚቃረኑ ተግዳሮቶች ምክንያታቸው ባዶና ስሕተትን የተላበሱ እንደሆኑ ምላሽን በመስጠት እረጋግጠናል። በእንዳሩ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ጽኑና የስውን ተግዳሮት ሁሉ ተቋቁሞ የሚኖር መሆኑንም ተገንዝበናል። በዚህ መሠረትም የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የመጨረሻና የበላይ እንደሆነ ተመልክተናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ስንል

ሥልጣኑ በእኛ በአማኞቹ ሕይወት ላይ በበላይነት ይገዛል ማለታችን ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን የበላይነት አለመቀበል ማለትም የእግዚአብሔርን የበላይነት አለመቀበል ማለት እንደሆነም መረዳት ይኖርብናል። ለመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የበላይነት እስከ የት ይደርሳል? ለምላሹ ቀጥለው ያሉትን እንመልከት።

ሀ. በሰው ሐሳብ ላይ የበላይ ነው /ምሳሌ 3:5-7፣ 19:21፣ 2ኛ ነገ 5:11-14፣ ኢሳ. 1:18፣ 55:8-9፣ ሮሜ. 12:1-2/።

ለ. በቤተ ክርስቲያን ላይ የበላይ ነው /ኤፌ.1:22፣ 2:19-20፣ ራእይ 2:4-5፣ 2:14-16፣ 2:20፣ 3:1-3፣ 3:15-19/።

ሐ. በትውፊት /Tradition/ ላይ የበላይ ነው /ማቴ.15:6፣ ቆላ. 2:8/።

መ. በመሪዎችና በሰባኪዎች ላይ የበላይ ነው።

ሠ. በስሜቶቻችንና በተሞክሮዎቻችን ሁሉ ላይ የበላይ ነው /መዝ. 27:13፣ 42:4፣ 77:1-10፣ 16:11/።

5. ለመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ራሳችንን የምናስገዛበት ምክንያት

ሀ. ከነሙሉ ሥልጣኑ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስለሆነ፤

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋስ መለኮት በመሆኑ ምክንያት /The Bible was Intially Received as God-Breathed/፤

ሐ. እስትንፋስ መለኮት ከመሆኑ የተነሣም ስህተትና እንከን የለሽ በመሆኑ /Inerrant/፤

መ. የመጽሐፍ ቅዱስ እስተምህሮ ንጹህ ከመሆኑም በላይ እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ መሆኑን ማረጋገጫ በመስጠቱና በዓለም ታሪክ ሂደት ስሰ ተከስቱ እንዳንድ ክስተቶችም የታመነ የመረጃ ምንጭ በመሆኑ፤

ሠ. የሰውን ሕይወት ከመለወጥ እኪያም መለኮታዊ የሆነ ኃይል በመያዙ፤

ረ. የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር እገልግሎቱ ዘመን ከቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት መጥቀሱና የሰውን ሕይወት ሰመምራት ሥልጣን ያሰው መሆኑን በማሳየቱ፤

ሰ. ሕይወታችንን በበሳይነት የመምራት መብትና ሥልጣን ያሰው በመሆኑ!

6. መጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ነው /The Bible is Revelation/

መገለጥ ሰመጽሐፍ ቅዱስ እመጣጥ እንጻር ሲተረጎም ከረጅም ጊዜ በፊት የተከሰተ ነገርን የሚጠቁም ሆኖ እናገኘዋለን። ይሁን እንጂ ውጤትም ነው። ውጤቱ ደግሞ በኋላ በሙሳት ግልጽ ሆኖ የወጣበትን ሁኔታም እመልካች ነው። በዚህ እገለለጽ መሠረት «መጽሐፍ ቅዱስ መገሰጥ ነው» ስንል እግዚአብሔር ስሱእሳዊነቱ ከዘሰዓለም በደነገገው መሠረት ጊዜው ሲደርስ ልዩ በሆነ መንገድ ሰሰዎች ራሱን በሙሳት ገልጦበታል ማሰታችን ነው። ወደዚህ ሙሳት የተደረሰው በታሪክ ሂደት ሰተሰያዩ ሰዎች በተሰያዩ መንገዶች ፈቃዱንና ሐሳቡን ሰመግለጽ የተናገረው ሁሉ እንዲጸፍ ትዕዛዝ በመስጠቱ ነው። በትዕዛዙ መሠረት በተጻፈው መጽሐፍም እግዚአብሔር ራሱንና የደህንነትን መንገድ ሰሰዎች በሙሳት ገልጿል። ይህም መጽሐፍ እግዚአብሔር ሰሰው ልጅ ያቀደውን መልካም ሐሳብና ዓላማ በሙሳት ይዞ የተገለጠ ጽሑፍ ነው። እንግዲህ ስው እርሱን ያውቀው ዘንድ እግዚአብሔር ራሱን በሙሳት የገለጠበት ጽሑፍ ሌላ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እውነተኛ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ምዕራፍ ሦስት

1. በታሪክ ሂደት እግዚአብሔር ለሰዎች የተናገረባቸው መንገዶች

ልጄን ልኮ ሰእኛ ከመናገሩ በፊት /ዕብ. 1:2/ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ሰተሰያዩ ሰዎች በተሰያዩ ጊዜያት በተሰያዩም መንገዶች ነቢያትን ጨምሮ ሲናገር እንደቆየ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል /ዕብ. 1:1/። እዚህ ላይ ነቢያት ሲል የብሱይ ኪዳን ጸሐፊዎችን ማለቱ ነው። ምስክርነታቸው የመሢሑን መምጣት የሚጠቁም ስለነበር ሁሉንም ከነቢያት ምድብ ጠቅልሏል። በዚህ መልክ ሲናገር ከቆየ በኋላ በብሱይ ኪዳን ዘመን ፍፃሜ ላይ ደግሞ በልጁ ስእኛ መናገሩን መጽሐፍ ቅዱስ ይፋ ያደርጋል /ዕብ. 1:2/። በታሪክ ሂደትም እግዚአብሔር ለተለያዩ ስዎች በተለያዩ ጊዜያት የተናገረባቸውን ስምንት ያህል መንገዶችን /Modes of Communication/ ቀጥለን እንመለከታለን።

ሀ. በመላእክት ለብዙ ጊዜ ተናግሯል

ዘፍ. 19

ዳን. 5 9:21-27

ማቴ. 28:5-7

ሉቃስ 1:11-20

ሉቃስ 1:26-27

ሉቃስ 2:8-14

የሐዋ. 5:26

የሐዋ. 12:7-18

ለ. ቀጥተኛ በሆነ ድምፅ ተናግሯል።

ዘፍ. 3:9-19 /አዳም ሆይ ወዴት ነህ/

ዘፍ. 6:13-21 /ኖህ/

ዘፍ. 12:1-3 /አብርሃም/

ዘጸ. 20:1-17 /ሙሴ በሲና ተራራ ላይ/

ኢያሱ 1:1-9 /ኢያሱ/

1ኛ ሳሙ. 3:1-14 /ሳሙኤል/

2ኛ ሳሙ. 7: 4-16 /ናታን/

1ኛ ነገ. 17:2-4 /ኤልያስ/

ኤር. 1:4-5 /ኤርምያስ/

ሐ. በሹክሹክታና ለስለስ ባለ ድምፅ ተናግሯል

1ኛ ነገሥ. 19:11-12

መዝ. 32:8 /አመክርሃሰሁ/

መ. በፍጥረት በኩል ተናግሯል

መዝ. 19:1-3 /ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ/

ሐዋ. 14:15-17

ሮሜ. 1:18-20

ሠ. በህያም እንደን ተናግሯል

ዘኁ. 22:28 «እግዚአብሔር የአህያይቱን አፍ ከፈተ በሰዓምንም አንዲህ አድርገህ ሶስት ጊዜ የመታሽኝ ምን አድርጌህ ነው?» አሰችው።

ረ. በተደጋጋሚ ጊዜ በሕልም ለሰዎች ተናግሯል

ዘፍ. 28:12
2ኛ ነገ. 3:5፣ 9:2
ማቴ. 1:20
ማቴ. 2:12
ማቴ. 2:19-22

ሰ. በራእይ ተናግሯል

ዘፍ. 46:2
1ኛ ዜና. 21:16
ኢሳ. 6:1-8
ሕዝ. 37
ዳን. 7:8
ዳን. 8
ዳን. 10:5-9
ሐዋ. 9:10
ሐዋ. 10:3-6
ሐዋ. 10:10-16
ሐዋ. 16:9
ሐዋ. 19:9
ሐዋ. 23:11

ሸ. (ክርስቶስ ራሱን በለው መልክ በገለጠ ጊዜ) በዚያ በኩል ደግሞ ተናግሯል

ዘፍ. 32:24-30
ዘፍ. 48:16
ዘፀ. 3:2
ዘፀ. 14:19
ዘፀ. 23:20-23
መሳ. 6:11
1ኛ ነገ. 19:7
ኢሳ. 37:36
ኢሳ. 63:9
ዳን. 3:25

እግዚአብሔር ከላይ በተገለጡት መንገዶች ያበተሳሰፈውን መልእክት ሰዎች በእበትንፋሰ መለኮት የበላይ ተቆጣጣሪነት /Inspiration/ በሰው ቋንቋ ጻፉት። እበትንፋበ መለኮት /Inspiration/ ስንል ምን ማለት እንደሆነ ጥናታችንን በቀጠልን ቁጥር እየተረዳን እንሄዳለን።

2. ግልጠተ-መለኮት /Revelation/

ግልጠተ-መለኮት /revelation/ ቀደም ሲል እንዳየነው በታሪክ ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ለሰው ልጆች ራሱን የገለጠበትን ልዩ ልዩ የሆኑ የመገለጥ መንገዶችን የሚያመላክት ነው። ከነዚህ የመገለጥ መንገዶች አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እግዚአብሔር ማንነቱን ለሰው ልጆች በሙሳት የገለጠበት ልዩ መገለጥ ነው።

3. አስትንፋስ መለኮት /Inspiration/

አስትንፋስ-መለኮት /Inspiration/ የመጣው "Theopneustos" ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። በቀላል አባባልም አስትንፋስ መለኮት/እግዚአብሔር

/God Breathed/ ማለት ነው። ይህም ቃል የእግዚአብሔርን የሕይወት አስትንፋስ መተንፈስን የሚያመለክት ነው /እግዚአብሔር አምላክ ከምድር አፈር ወስዶ ሰውን አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት አስትንፋስ እፍ አለበት፣ ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ ዘፍ. 2:7/። በሌላ መልኩ ደግሞ /Inspiration/ ከተፈጥሮ የለተነፋፈስ ሥርዓት ጋር የሚያያዝ ሆኖ እናገኘዋለን /The Act of Drawing and Inhaling Air/።

"Inspiration" ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በተገናኘ መልኩ የሚኖረው ትርጉም ደግሞ፣ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች መጽሐፉን ያሰምንም ስሕተት መጻፍ እንዲችሉ በመንፈሱ አለምሮአቸውን፣ ፈቃዳቸውን፣ ስሜታቸውንና አስተሳሰባቸውን በበላይነት የተቆጣጠረበት የቁጥጥር ሂደት ነው። ይህ ሲባል ግን እግዚአብሔር የጸሐፊዎችን ቃላትና አስተሳሰብ አልተጠቀመም ማለት አይደለም። ይልቁንም የቃሉን እውነት ለመግለጥ የግል ልምምዳቸውን ሁሉ ሳይቀር ተጠቅሞበታል /ፊል. 3:4 – 11/። በዚህ

ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርም የሰውም ሥራ ነው ሰማለት እንችላለን። ስለሆነም እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል የበላይ ተቆጣጣሪ በመሆን የእውነት ቃል እንዲፃፍ አደረገ /1ኛ ተሰ. 2:13/ /2ኛ ጴጥ. 1:20–22/ እንጂ የጸሐፊዎችን ቋንቋ፣ አስተሳሰብና ልምምዳቸውን አላገለሰም። እንዲያውም እግዚአብሔር ቃሉ በጽሑፍ እንዲሠፍር ሲፈቅድ ሰዎችን በመሣሪያነት እንደተጠቀመ መረዳት ይኖርብናል። ይህን ሲያደርግ ግን የቃሉ እውነት ሳይዛባ እውነተኝነቱን እንደጠበቀ ይፃፍ ዘንድ በመንፈሱ የበላይ ተቆጣጣሪነት የብለይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት እንዲፃፉ አድርጓል።

እግዚአብሔርም ፈጽሞ የማይዋሽና ሊሳሳት የማይችል አምላክ በመሆኑም /ዕብ. 6:18/ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እውነት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም ይህን እውነት በማረጋገጥ ሲጽፍ «ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው። ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት፣ በጽድቅም መንገድ ለመምከር፣ ይጠቅማሉ። ይኼውም የእግዚአብሔር ሰው ሰመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው» /2ኛ ጢሞ. 3:16–17/ በማለት በእጽንኦት ገልጿል። ከዚህ ክፍል ጋር አያይዘን ማወቅ የሚገባን ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ያለቀ ስለሆነ በላዩ ላይ መጨመር ወይንም መቀነስ የማይቻል መሆኑን ነው። ይህን ማሳሰቢያ በማይሰማ ላይ የእግዚአብሔር እርግማን እንደሚወድቅበትም ተጽፏል /ራእይ 22:18–19/።

4. አብርሆተ መለኮት /Illumination/

አብርሆተ መለኮት ማለት ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈውን የእግዚአብሔርን እውነት ይረዱ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ለእነርሱ የሚያበራበት/የሚያስረዳበት ሂደት ነው። በዚህን ጊዜ ማስተዋል የሚገባን ነገር ግልጠተ- መለኮት /Revelation/፣ አስትንፋስ መለኮት /Inspiration/ እና አብርሆተ መለኮት /Illumination/ ሶስቱም

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆናቸውን ነው /ሉቃስ 24:26-27፣ 44-45፣ 1ቆሮ. 2:11-14፣ ዮሐ. 16:12-15፣ የሐዋ. 17:1-3/፣ በአጭር አገላለጽ ግልጠተ-መለኮት ማለት /Revelation/ እውነት የሚገለጥበት መንገድ ነው፤ አስትንፋሰ-መለኮት /Inspiration/ ደግሞ የእውነት ዘገባ /The Recording of Truth/ ሲሆን አብርሆተ-መለኮት ስንል ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ አርዳታ የተዘገበውን ቃለ እግዚአብሔር መረዳት ማለት ነው /1ኛ ዮሐ 2:20,27/። በአጠቃላይ መንፈስ ቅዱስ የግልጠተ መለኮት፣ የአስትንፋሰ መለኮት እና የአብርሆተ መለኮት የበላይ ወኪል ነው። ይህም ኢየሱስ የገባልንን ተስፋ የሚያመለክት ነው /ዮሐ. 15:26፣ 16:12-13/።

5. የአብርሆተ መለኮት አስፈላጊነት /Need for Illumination/

አብርሆተ መለኮት በሁለት ምክንያቶች ያስፈልገናል። አንደኛው ምክንያት እኛ የሰው ልጆች ውስኖች ስለሆንን ወሰን የሌለውን አምላክ በውስን አዕምሮአችን ማስተዋል ከአቅማችን በላይ በመሆኑ ነው። ስለሆነም ጠሊቅ የሆነውን መንፈሳዊ ነገር ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስ አርዳታ በእጅጉ ያስፈልገናል። አብርሆተ መለኮት ካላገኘን ክራሳችን አይታ ከልል መውጣት አንችልም። መጽሐፍ ቅዱስም ይህን እውነት አስመልክቶ እንዲህ በማለት ያውጃል «መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳን ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል።» በውስጡ ካለው ክራሱ መንፈስ በስተቀር ከሰው ማን አለ? እንደዚሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ በስተቀር የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚያውቅ ማንም የለም /1ቆሮ. 2:11/ ይላል። ሌላው ቀርቶ አንድ ሰው በኮሌጅ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስን ዋና ትምህርት አድርጎ የሚማር ቢሆን እንኳ መንፈስ ቅዱስ ክልረዳው በስተቀር የመጽሐፉ መንፈሳዊ ትርጉም ሲገባው አይችልም።

ሁለተኛው ምክንያት ኃጢአት የሰውን ልብ ክእግዚአብሔር በመለየቱ ነው። ከዚህ የተነሣም መንፈሳዊ ሕይወቱ በጨለማ ተዋጠ /ሮሜ. 1:21፣ ኤፌ. 4:18፣ 5:8፣ የሐዋ. 26:18፣ ሮሜ. 2:19፣ ዮሐ. 1:5፣ ቆላ.1:13/። እነዚህና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አብርሆተ-መለኮት ከእግዚአብሔር ክብርና ፀጋ ለወደቀ ሰው እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታሉ። በተጨማሪም ሰው መንፈሳዊ ነገሮችን ስማስተዋል አቅም የሌለው መሆኑንም ይገልጣሉ። ሆኖም ዳግመኛ ሲወለድ በመንፈሱ ትንሣኤን ያገኛል። የእግዚአብሔርንም ነገር ለመረዳት ስሜቱና የውስጥ ሰውነቱም ንቁ ይሆናል።

አዲስ ፍጥረት /2ኛ ቆሮ. 5:17/ ስመሆኑም ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ነገር በመረዳት ማደግ ይጠበቅበታል። ይህ የተሳካ እንዲሆን የሚያስፈልገው ግልጠተ-መለኮት ብቻ ሳይሆን ቃሉን መረዳት የሚያስችለውን አብርሆተ-መለኮትም ጭምር ነው። አብርሆተ መለኮት ደግሞ የተወለደው ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ይረዳ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ለርሱ የሚያስረዳበት ሂደት ስለሆነ እጅግ አስፈላጊ ነው።

አንድ አማኝ ማስተዋል ያለበት ነገር ቢኖር አብርሆትን ለስንፍናው ምክንያት አድርጎ መጠቀም እንደሌለበት መሆኑን ነው። ይኼውም እኔ ያለ አብርሆት ፈጽሞ ሊገባኝ ስለማይችል መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ አልሞክርም ማለት እንደሌለበት ነው። ለምን ቢባል እግዚአብሔር የሰጠውን የአእምሮ የመረዳት ችሎታ ተጠቅሞ የድርሻውን ማድረግ ይችላልና ነው። <u>ለምሳሌ</u>፡ አንድ ቃል ካላወቀ መዝገበ ቃላትን ማየት ይችላል። ስለዚህ ኮሜንታሪን፣ የጥቅስ ማውጫን፣ እንዲሁም ደግሞ መዝገበ ቃላትን፣ ከመጠቀም ይልቅ መንፈስ ቅዱስ የግድ ትርጉሙን እንዲስጠው መጸለዩ መንፈስ ቅዱስን ለራሱ ጥቅም ማድረግ እንዳይሆንበት መጠንቀቅ አለበት። ነገር ግን የመልእክቱን ጥቅም እንዲያሳየውና ለተግባራዊነቱም አቅም እንዲያገኝ መፀለዩ እጅግ አስፈላጊና ተገቢም ነው።

6. የተለያዩ የእስትንፋሰ መለኮት ቲዎሪዎች (አመለካከቶች) /The Theories of Inspiration/

በዚህ ርዕስ ስር ስምንት የለያዩ የእስትንፋሰ መለኮት አመለካከቶችን እንዳበላለን።

ሀ. የተሟላ እስትንፋሰ መለኮት ቲዎሪ (አመለካከት) /The Plenary (complete or full) Theory of Inspiration/

ይህ አመለካከት ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በአኩል ደረጃ እስትንፋሱ-እግዚአብሔር ናቸው ብሎ የሚያምን ቲዎሪ (አመለካከት) ነው። ስዚህ ድምዳሜም መሠረቱ 2ጢሞ. 3:16 ነው። በተጨማሪም አመለካከቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በአጻጻፍ ሂደት በእስትንፋሰ መለኮት ተመርተዋል የሚለውን እውነት ተቀባይ ነው። በዚህ ረገድም አግዚአብሔር አንዲተላለፍ የፈለገውን ግልጽና ትክክለኛውን መልእክት አስተላልፏል ብሎ ያምናል። ደግሞም የመልእክቱ ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑንና ይህንንም መልእክት በጸሐፊዎቹ ላይ እንደተነፋሰ ያስምርበታል። የጸሐፊዎቹ ድርሻ ደግሞ ይህን የእግዚአብሔርን መልእክት በአእምሮአቸው፣ በልምምዳቸው፣ በቋንቋቸው፣ በባህላቸውና አምላካዊ ስጦታ በሆነ ጥበባቸው በመጠቀም መግለጽ ወይንም መጻፍ እንደሆነ ይቀበላል። ይህ አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ተቀባይነት ያለው ነው።

ለ. የተፈጥሮአዊ እስትንፋሰ መለኮት ቲዎሪ (አመለካከት) /The Natural Theory of Inspiration/

ይህ አመለካከት ሳቅ ያለ የተፈጥሮአዊ ስው የማስተዋል ችሎታ በግብረገብና በኃይማኖታዊ እውነት ላይ የመንፀባረቅ ሁኔታ ነው ይላል። በመሆኑም ምንም ዓይነት መለኮታዊ የሆነ ነገር የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችን የበላይ ሆኖ አንዳልተቆጣጠራቸው የሚያምን ነው። እንዲያውም መጽሐፍ

ቅዱስ ልዩ የሆነ የአእምሮ ችሎታ ያላቸው ሰዎች የፈጠራ ውጤት ነው በማለት ያስምርበታል። ሲደመድምም መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ሥራ ውጤት እንጂ ሌላ አይደለም ይላል።

ሐ. ከፊል እስትንፋሰ መለኮት /Partial Inspiration/

በዚህ አመለካከት መሠረት አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በእግዚአብሔር ሙሉ ሰሙሉ የተተነፈሱ /Fully God Breathed/ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በከፊል ብቻ በእግዚአብሔር የተተነፈሱ /Partially God Breathed/ እንደሆኑና የተቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ግን ፈጽሞ በእግዚአብሔር እንዳልተተነፈሱ የሚያምን አመለካከት ነው።

በዚሁ አመለካከት ሥር የሚመደቡ ሌሎች ሰዎች ደግሞ በእግዚአብሔር አብና በኢየሱስ በቀጥታ የተነገሩ ቃላት በደቀ መዛሙርቱ ከተነገሩት ቃላት የበለጠ በእግዚአብሔር የተተነፈሱ ናቸው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት መንፈሳዊና አስተምሮተ አምነት በእግዚአብሔር የተተነፈሱ መሆናቸውን ይቀበላሉ። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፈው የሚገኙትን ታሪካዊ፣ ሥነ መልክአ ምድርና ከሳይንሳዊ ነክ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሁሉ በእግዚአብሔር አንዳልተተነፈሱ ይደነግጋሉ። ይህ አመለካከት የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ብቻ በእግዚአብሔር ቃልነት የሚቀበል ስለሆነና ከ2ጢሞ. 3:16-17 ካለው ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም።

የዚህ አመለካከት ዋና ችግር ሰስብአዊ ፍጡር የመጽሐፍ ቅዱስን አጣ ፈንታ እንዲወስን ሥልጣን መበጠቱ ነው። ስለሆነም በዚህ አመለካከት አራማጆች አስተሳሰብ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት፣ ዓላማና ምንነት የማይታወቅ ነው። አለመታወቁ ብቻም ሳይሆን ይህ እውነት ለአነርሱ በግለሰቦች

ስሜትና አስተሳሰብ መሠረት የሚወሰን ነገርም ነው። ይህም ጽንሰ ሐሳብ የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር እንደተተነፈሰ ይወስን ዘንድ ለሰው ሥልጣን መስጠቱን አመልካች ነው። በዚህ አመለካከት አንጻርም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ለሁሉ ለሰው የሚታይ እውነት አይደለም። ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በሰው ብያኔ/ውሳኔ ላይ የሚደገፍ እንጂ በራሱ የሚቆም አይደለም። በአጠቃላይ ይህ አመለካከት የእምነታችንና የኑሮአችን መመሪያ በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለንን መታመን/እምነት የሚደመስስ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም።

መ. የቃል በቃል ግልበጣ ቲዎሪ (አመለካከት) /The Mechanical Dictation Theory of Inspiration/

የዚህ ጽንሰ ሐሳብ አመለካከት የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲያን እግዚአብሔር ቃል በቃል የተናገራቸውን ብቻ የጻፉ የእግዚአብሔር ጸሐፊዎች ናቸው የሚል ነው። ለአቋማቸው ድጋፍ የሚጠቅሱት ጥቅስ፡ ከዚያም እግዚአብሔር መሴን «እነዚህን ቃሎች ጻፋቸው፤ በእነዚህ ቃሎች መሠረት ከአንተና ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጌአለሁና» /ዘጸ. 34:27/ አለው የሚለውን ነው ::

የዚህ ጽንሰ ሐሳብ ድክመት የመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር የጸሐፊዎቹን ስብዕና፣ ቃላት፣ ዳራ፣ ጥበብና ልምምዳቸውን ሁሉ መጠቀሙን መካዱ ነው። ለዚህ ይህ ጽንሰ ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጠው ማስረጃ ጋር የሚመሳሰል ስላልሆነ አንቀበለውም።

ሠ. የአብርሆተ መለኮት ጽንሰ አሳብ ቲዎሪ (አመለካከት) /The Illumination Theory of Inspiration/

በዚህ አመለካከት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ የአብርሆተ መለኮት /Ilumination/ ውጤት ነው። ማለትም በዚህ ዘመን ያሉት አማኞች አብርሆተ-መለኮትን እንደሚያገኙና በፍጥነት እንደሚንቀሳቀሱ ብሎም በመንፈስ ቅዱስ እንደሚቀቡ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችም ዘንድ የነበረው ሁኔታ ተመሳሳይ ነበረ ማለት ነው። ይህ ቲዎሪ በተዘዋዋሪ ማለት የፈለገው መጽሐፍ ቅዱስ የለው የመረዳት ችሎታ ውጤት እንደሆነ ነው።

በመሠረቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ግልጠተ-መለኮት /Revelation/፤ እስትንፋሰ መለኮትና /Inspiration/ በዚያው ልክ ደግሞ አብርሆተ-መለኮት /Illumination/ የነበራቸው ነበሩ /የሐዋ. 13:27፣ መዝ. 119:18/። ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ የለው የመረዳት ችሎታ ውጤት አለመሆኑን አበክሮ መገንዘብ ያሻል።

ረ. የአሳብ እስትንፋሰ መለኮት ቲዎሪ (አመለካከት) /The Concept Theory of Inspiration/

የዚህ አመለካከት አቋም እግዚአብሔር የመጽሐፉን አጠቃላይ ሐሳብ ለጸሐፊዎቹ ሰጣቸው፤ እነርሱ ደግሞ በራሳቸው ቃል አቀነባብረው ጻፉት የሚል ነው። ይህ አመለካከት ተፈላጊው አጠቃላይ ሐሳቡ እንጂ ሐሳቡ የተገለጠበት ቃል ምንም ይሁን ምን ችግር የለውም ይላል። እንዴታ! የቃሉ ትክክለኝነት ካልተረጋገጠ እንዴት ትክክለኛ ሐሳብ ይኖራል? ይህ ቲዎሪ ከቃሉ አንዳች ነጥብ አትወድቅም የሚለውን የጌታን ቃል ድንጋጌ የሚጥስ ስለሆነ ተቀባይነት አይኖረውም።

ሰ. የዓላማ ጽንሰ ሐሳብ ቲዎሪ (አመለካከት) / The Purpose Theory of Inspiration/

በዚህ አመለካከት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ሲታረቁ የማይችሉትን ቅራኔዎች ይዟል። ይሁን እንጂ በትምህርቱ ሙሉነት /Doctrinal Integrity/ የእግዚአብሔርን ዓላማ ማስተላለፍ የሚችል እንደሆነም ይቀጥራል። በዚህ ጽንሰ ሐሳብ አመኔታ መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ ስህተት አልባነት በታሪካዊ እውነትነቱና በይዘቱ ሳይሆን በአጠቃላይ ትምህርቱና ዓላማው ነው። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር የማዳን ዓላማ በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት በማከናወኑ ምክንያት እንቀበለዋለን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የዘገባቸውን ታሪካዊ እውነቶች ሁሉ እንቀበልም ባይ ነው። የጽንሰ ሐሳቡ አመክንዮ ታሪካዊ እውነት ሰሥነ መለኮታዊ እውነት መሠረት መሆኑን የዘነጋ ነው።

ሸ. የመቻቻል እስትንፋስ መለኮት ቲዎሪ (አመለካከት) /The Accommodation Theory of Inspiration/

የዚህ አመለካከት አካሄድ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችን ድካም ያህል ራሱን ገድቧል ነው። ጸሐፊዎቹ በባህሳቸው፣ በዖታቸው፣ በቃላታቸውና በአእምሮ ችሎታቸው የተወሰኑ በመሆናቸው ምክንያት እግዚአብሔር ይህን ማንነታቸውን አልፎ መሥራት አልቻሰም ይላል። ጽንሰ ሐሳቡ አቢይ ነጥብ እግዚአብሔር ሰማስተላለፍ የሚፈልገውን

መልእክት ጸሐፊዎቹ አይረዱስትም የሚል ነው። የሚረዱ ቢሆኑ እንኳ በራሳቸው ቋንቋ በሚገባ አይገልጡትም ይላል። ሲደመድምም፦ እንዲያው ብቻ ስለ እግዚአብሔርና ስለ እውነት የገባቸውን ያህል ጽፈዋል በማለት ያስቀምጣል። የዚህ ጽንሰ ሃሳብ ማሳረጊያ ነጥብ ጸሐፊዎቹ ውስን ከመሆናቸው የተነሳ የእግዚአብሔርን እውነት አዛብተዋል ነው። ይህ አመለካከት

የእግዚአብሔርን የአሳቡን የመግለጽ ችሎታውን ዝቅ የሚያደርግ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር አሳቡን በመግለጽ ተወዳዳሪ የማይገኝለት አምላክ ስለሆነ ነው።

ማሳሰቢያ

በተራ ቁጥር 1 ከተጣፊው አመለካከት በስተቀር የተቀሩት ሁሉ ስህተትን ያቀፉ ጽንሰ ሐሳቦች ናቸው።